# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን
## የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት የሥራ አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ  የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት





ሚያዚያ 2017
አዲስ አበባ

*ማውጫ*


የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ I

(Executive Summery) I

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

የኮሚሽኑ አመሰራረት ....1

የኮሚሽኑ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴት፣ ዓላማ፣ ስልጣንና ተግባር....2

*ራዕይ* 2

*ተልዕኮ* 2

የኮሚሽኑ ዓላማ....2

የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር ....2

የኮሚሽኑ አደረጃጀትና የሰው ኃይል....4

*የኮሚሽኑ አደረጃጀት* 4

*የሰው ኃይል* 4

የኮሚሽኑ የፋይናንስ ምንጭ ....5

የኮሚሽኑ ሰብዓዊ እርዳታ/ድጋፍ/ ሥርጭት አተገባበር የስራ ፍሰት....5

የኦዲቱ ዓላማ፡- ....7

የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ....7

*የኦዲት ወሰን* 7

*የኦዲት ዘዴ* 7

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) ....8

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ....8

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ....8

ክፍል ሁለት 10

የኦዲት ግኝቶች 10

ለመጠለያ ጣቢያዎች (ተፈናቃዮች) የሚላከው የእርዳታ እህልና ቁሳቁስ የሰብዓዊ እርዳታ ፈላጊ ቁጥርን ያገናዘበ መሆኑን በተመለከተ። ....10

**ኮሚሽኑ የሰብዓዊ ዕርዳታ ሲያሰራጭ አጥቢ፣ ነብሰ ጡር እናቶችና ህፃናት የተመጣጠነ ምግብ ማግኘታቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑን በተመለከተ፡፡** 12

**በመጠለያ ጣቢያዎች መሠረታዊ መሰረተ ልማት መሟላታቸውን በተመለከተ** 15

**ኮሚሽኑ በሃገሪቱ በሚገኙ በሁሉም መጠለያ ጣቢያዎች መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡** 15

**በኮሚሽኑ አስፈላጊ የሆኑ የትራንስፖርት እና የሎጅስቲክስ አቅርቦት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፡፡** 18

**ኮሚሽኑ የቅድሚያ ቅድሚያ ትኩረት የሚገባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ለመለየት የሚያስችል መስፈርት በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣** 20

**ኮሚሽኑ ለሰብዓዊ እርዳታ የሚውሉ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ጥራታቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑን በተመለከተ** 23

**ኮሚሽኑ በቋሚነት ለሰብዓዊ እርዳታ ስራ የሚውል ፈንድ መቋቋሙን በተመለከተ፡፡** 25

ኮሚሽኑ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ አነስተኛ ክምችት የሚያዝበት ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ

ያደረገ መሆኑን በተመለከተ። 27
ኮሚሽኑ በተለያዩ መጋዘኖች የሚገኝ ክምችትን ከብልሽት የሚከላከልበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ። 29
ኮሚሽኑ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ። 32
በኮሚሽኑ የሚከናወኑ የመጋዘን ግንባታዎች በተመለከተ። 34
ኮሚሽኑ የእርዳታ እህልና ቁሳቁስን ያለ አግባብ ላልተገባ ዓላማ እንዳይውል ለመከታተል የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ። 39
ኮሚሽኑ የየአመት ዕቅድ አፈፃፀሙን ከባለድርሻ ፣ ከአጋር አካላት ፣ ከክልሎች እና ከተረጂ (ተፈናቃይ) ወገኖች ጋር በጋራ መገምገሙን በተመለከተ። 40
ኮሚሽኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን ለማጓጓዝ የትራንስፖርት አገልግሎት ግዥ አፈጻጸምን በተመለከተ፣ 42
ክፍል ሶስት 44
መደምደሚያ 44
ክፍል አራት 47
የማሻሻያ ሃሳቦች 47
አባሪ 1: ተቋማዊ መዋቅር i
አባሪ ሁለት፡ የመመዘኛ መስፈርቶች ii
አባሪ 3፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የመስክ ጉብኝት የተደረገባቸው እና በኢሜል መጠይቅ የቀረበላቸው v
አባሪ 4 -የተከለሱ ሰነዶች vi
አባሪ 5፡ የመጠለያ ጣቢያዎችና የተረጂ ወገኖች ብዛት በክልል vii
አባሪ 6፡ የመጠለያ ጣቢያዎችና የተረጂ ወገኖች ብዛት በዕድሜ vii
አባሪ 7. ዕድሜያቸው ከ0-4 የሆኑ ተፈናቃይ ህጻናት ብዛት በክልል viii
አባሪ 8፡ ለመጋዘን ግንባታ የተመደበ የካፒታል በጀት ix
አባሪ 9፡የካፒታል በጀት አፈፃፀም x

# የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ


## (Executive Summery)


የአደጋ ክስተቶች በባህሪያቸው ዘርፈ-ብዙና አደጋዎችንም ለመመለስም ይሁን ለመከላከል የብዙ ተቋማትና ማህበረሰብ ተሳትፎ፣ ልምዶችና እውቀቶችን የቀጥታ የባለቤትነት ተሳትፎ የሚፈልግ ትልቅ ስራ ነው። የአደጋ ባህሪ ይህ በመሆኑ ለአደጋዎች ምላሽ ለመስጠትና ለመከላከል የተለያዩ አካላት ሚናቸውን እንዲወጡ ከአስተሳሰብ ማስተካከል ጀምሮ እስከ በባለቤትነት ስራውን በእቅድ፣ በአደረጃጀትና በአሰራር በጋራ ለመምራት ሰፊ ስራ የሚጠይቅ ነው።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ-መንግሥት አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት መንግስት አደጋ እንዳይደርስ የመከላከል፤ ሲደርስም ወቅታዊ ምላሽ የመስጠት እና የዝግጁነትና ምላሽ ስርዓትን መገንባት ተቀዳሚ ኃላፊነቱ ነው። ስለሆነም ኮሚሽኑ ይህንን ዓላማ ምን ያህል እያሳካ እንደሆነ ለማወቅ መ/ቤታችን በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን "የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት አፈፃፀም" በሚል ርዕስ የክዋኔ ኦዲት አከናውኗል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፉ እና በኢትዮጵያ የክዋኔ የኦዲት ስታንዳርድ እንዲሁም ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ሲሆን፤ በኦዲቱ ወቅት የተገኙት ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርቧል

☞ በ2016 የተረጂዎች ልየታ ጥናት መሰረት ወደ 2738 የሚጠጋ መጠለያ ጣቢያዎች የውስጥ ተፈናቃዮች ብዛት 3,306,698 የነበሩ ሲሆን ነገር ግን የተመደበው የሰብአዊ ዕርዳታ እየቀረበላቸው አለመሆኑ፣




☞ በ2016 የተረጂዎች ልየታ ጥናት መሰረት በሃገሪቱ የሚገኙ ከአምስት ዓመት በታች ተረጂ ህፃናት ቁጥር 489,290 (ከአጠቃላይ ተረጂ 15 ፐርሰንት) የሚገኙ

ቢሆንም የተጨማሪ አልሚ ምግብ (በቆሎና አኩሪ አተር ቅይጥ CSB (corn, soya & bean) ከአምስት አመት በታች ላሉ ህፃናት፣ ለአጥቢና ነፍሰጡር እናቶች ብቻ መሰጠት የሚገባው ቢሆንም ለሁሉም ተረጂዎች ያለ ምንም ተጨማሪ መስፈርት እንዲሰጥና በአፋጣኝ እየተተካ አለመሆኑ፣

☞ መብራት፣ ውሃ፣ የመታጠቢያ ቤት ወይም የመጸዳጃ አገልግሎት፣ የህክምና አገልግሎት የሌላቸው መጠለያ ጣቢያዎች መኖራቸው፣

☞ ለከፍተኛና ለዘርፈ-ብዙ አደጋዎች አስፈላጊ የሆኑ ሎጀስቲክስ/ ሄሊኮፕተር፣ ማሽነሪዎች (ዶዘር፣ ኤክስካቫተር)፣ ጀልባዎች፣ ወዘተ የመሳሰሉ መሳሪያዎች በኮሚሽኑ እንዲሁም በክልል አደጋ ስጋት አመራር ቢሮዎች የማይገኙ መሆኑ፣ ወይንም ሲያስፈልጉ ከሌሎች አካላት በውሰትም ሆነ በኪራይ የሚያገኙበት ስትራቴጂ እና ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣

☞ ለአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ፈንድ በቋሚነት የሚቋቋበትን ሁኔታ ኮሚሽኑ ጥናት ያላከናወነ መሆኑና በዕቅድ የያዛቸው የሀብት ማሰባሰቢያ ሥራዎች ያላከናወነ መሆኑ፣

☞ ኮሚሽኑ ባሉት መጋዘኖች ውስጥ ሆነ በክልሎች መጋዘኖች ውስጥ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ አነስተኛ ክምችት (Minimum Stock) የሚያዝበት ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ ፣

☞ የቅድመ ማስጠንቀቂያ የክስተት ሁኔታ መምሪያ ቴክኖሎጂዎችና የኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች ገና በዝግጅት ደረጃ የሚገኙ እና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ቴክኖሎጂዎችና ኮሚኒኬሽን መሣሪያዎች ያልተገጠመላቸው ክልሎች መኖራቸው፣

☞ በኮሚሽኑ እየተከናወኑ ያሉ የቀብሪዳሃር፣ የፍኖተሰላም እና የሆሳዕና የመጋዘን ግንባታዎች በተያዘላቸው ጊዜ እና በጀት እየተከናወኑ ባለመሆኑ መንግስትን ተጨማሪ 9,094,417,387.08 (ዘጠኝ ቢሊዮን ዘጠና አራት ሚሊዮን አራት መቶ አስራ ሰባት ሺ ሶስት መቶ ሰማንያ ሰባት) ብር ወጪ እንዲያወጣ አድርጓል፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ከላይ ለተመለከቱት ዋና ዋና ግኝቶች መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

☞ ኮሚሽኑ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ወገኖች የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት ተደራሽ መሆኑን ለማረጋገጥ በየዓመቱ በዕቅዱ ውስጥ በማካተት ትኩረት ሰጥቶ የማረጋገጥ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ኮሚሽኑ ለክልሎች የሚላከው የእርዳታ እህልና ቁሳቁስ በተጠናው የሰብዓዊ እርዳታ ፈላጊ ቁጥርና በቀረበው ፍላጎት መሰረት

የተሰራጨ መሆኑን እንዲሁም የሰብዓዊ እርዳታው ለተፈለገው አካባቢ መድረሱንና ለታለመለት ዓላማ መዋሉን የድጋፍና የቁጥጥር ስራ በመስራት ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

☞ ኮሚሽኑ የተጨማሪ አልሚ ምግብ (በቆሎና አኩሪ አተር ቅይጥ CSB (corn, soya & bean) ከአምስት አመት በታች ያሉ ህፃናትን፣ የአጥቢና የነፍሰጡር እናቶችን በበቂ ሁኔታ የሚያገኙበት እንዲሁም አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጥሮ ተጨማሪ መስፈርት ለሌሎች ተረጂዎች ከተከፋፈለ መልሶ የሚተካበት አሠራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግና ተግባራዊነቱን ኮሚሽኑ ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ የክትትልና የድጋፍ ስራውን በማጠናከር ወደ ክልሎች የሚላኩ እርዳታዎች ለሌላ ዓላማ እንዳይውሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ሊሰራና ሊከታተልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

☞ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በኦሮሚያ ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሮጉቱ እና ደደር ወረዳ የሚገኙ ባልታዩት እና ተመሳሳይ ችግር ያለባቸው የመጠለያ ጣቢያዎች ተፈናቃይ ወገኖች መብራት፣ ውሃ፣ ሽንት ቤት አገልግሎት እና መጠለያ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊሰራ ይገባል፡፡ የህክምና አገልግሎት የሌላቸው መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ ተፈናቃይ ወገኖች የህክምና አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አሰራር ሊዘረጋና መተግበሩን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

☞ ከፍተኛና ለዘርፈ-ብዙ አደጋዎች አስፈላጊ የሆኑ ሎጀስቲክስ/ ሄሊኮፕተር፣ ማሽነሪዎች፣ ጀልባዎች፣ ወዘተ የመሳሰሉ መሳሪያዎች ሲከሰቱ በአፋጣኝ ለማቅረብና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ፣ በኮሚሽኑ እንዲሁም በክልል አደጋ ስጋት አመራር ቢሮዎች ደረጃ እንዲሟሉ ወይም ለአገልግሎት ሲያስፈልጉ ከሌሎች አካላት በውስትም ሆነ በኪራይ የሚገኙበት ስትራቴጂ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

☞ ኮሚሽኑ እንደ አገር በራስ አቅም ችግሮችን ለመቋቋም የሚረዳ ሀብት ለማሰባሰብ በጥናት ላይ የተመሰረተ ለድንገተኛ አደጋ መከላከያ ሥራ የሚውል ፈንድ ለማቋቋም የመነሻ ሃሳብ ሊያዘጋጅና ለሚመለከተው አካል በማጸደቅ ሊያቋቁም ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ሃብት የማሰባሰብ ሥራ በማከናወን ከውጭ ለጋሽ አካላት ከሚገኘው ድጋፍ በተጨማሪ በአገር ውስጥ ሀብት በቋሚነት የሚሰበስብበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግና ኮሚሽኑ

በ10 ዓመቱ (2013-2022) መሪ ዕቅድ መሰረት ሀብት ማሰባሰብ ይጠበቅበታል፡፡

☞ ኮሚሽኑ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ አነስተኛ ክምችት የሚያዝበት ስርዓት ዘርግቶ በራሱም ሆነ በክልል አደጋ ስጋት መጋዘኖች ተግባራዊ እንዲደረግ ሊያደርግ ይገባል፡፡

☞

ቅድመ ማስጠንቀቂያ የክስተት ሁኔታ መምሪያ ቴክኖሎጂዎችና የኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች ገና በዝግጅት ደረጃ የሚገኙ የቅድመ ማስጠንቀቂያ የክስተት ሁኔታ መምሪያ ቴክኖሎጂዎችና የኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች፣ የ Situation room ግንባታ ወደ ሙሉ ትግበራ እንዲገቡ ሊደረግ የሚገባና እና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ቴክኖሎጂዎችና ኮሚኒኬሽን መሣሪያዎች ያልተገጠመላቸው ክልሎች ዕቅድ ተይዞላቸው ሊሟላላቸው የሚገባና በሁሉም የአገሪቱ ክልልች የቅድመ ማስጠንቀቂያ ትግበራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተደግፎ ሊከናወን ይገባል፡፡

☞

ኮሚሽኑ የቀብሪዳሃር ፣ የፍኖተሰላም እና የሆሳዕና የመጋዘን ግንባታዎች በተያዘላቸው ጊዜ እና በጀት እንዲጠናቀቁና ከተቋራጮችና ከአማካሪ ድርጅቶች ጋር ያጋጠሙ ችግሮች ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር እንዲፈቱ በማድርግ እና በተገባው ውል መሰረት ስራው እየተሰራ ስለመሆኑ ተገቢውን የድጋፍና የክትትል ስራ ሊሰራ እና ለታለመላቸው ዓላማ አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡

ኮ

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ኢትዮጵያ የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ የአየር ንብረት ለውጥ ባለፉት አመታት ውስጥ በተደጋጋሚ አጋጥሟታል፡፡ ከተከሰቱት አደጋዎች ውስጥ ተደጋጋሚ የጎርፍ፣ የድርቅና የበረሃ አንበጣ መከሰት እንዲሁም ግጭቶች ይገኙበታል፡፡ በዚህም ምክንያት ሰዎች ከመኖሪያ ስፍራቸው እየተፈናቀሉ፣ እንዲሁም የግብርና፣ የደን ጥበቃ፣ የጤና እና በሌሎችም ዘርፎች ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ መፍጠሩና የልማት ስራዎች ወደኋላ የተጎተተ እንዲሆን አድርጎታል።

2. በመሆኑም በዚህ ችግር ተጠቂ የሆኑትና ከመኖሪያ ሥፍራቸው ለተፈናቀሉት ዜጎች የሚያስፈልጋቸውን ሰብአዊ እርዳታዎች እንዲያገኙ፣ ወደ ቀድሞው መኖሪያቸው ተመልሰው እና በዘላቂነት ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡ ይህን ዕርዳታና ድጋፍ ሥራ የሚያስተባበርና የሚመራ ተቋምና በየደረጃው አደረጃጀት መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡

## የኮሚሽኑ አመሰራረት

3. በኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜያት በነበሩ ተከታታይ የድርቅ ክስተቶች በሀገሪቱ ላይ ለደረሰው ችግር መፍትሄ ለመፈለግ በየአስተዳደር ስርዓቱ እና ዘመኑ መጠነኛ እንቅስቃሴዎች የነበሩ ቢሆንም፣ ነሀሴ 23 ቀን 1966 ዓ.ም የእርዳታ ማስተባበሪያና መቋቋሚያ ኮሚሽን በአዋጅ ትዕዛዝ ቁጥር 96/66 ዓ.ም ለደረሰው ችግር መፍትሄ ለማፈላለግ እንደገና ለማቋቋምና ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር የሚገኘውን ድጋፍ ለማስተባበር ተቋቋመ፡፡ በመቀጠልም በአዋጅ ቁጥር 173/1972 ህጋዊ መብትና የስራ ኃላፊነት ተሰጥቶ ተቋቋመ፡፡
4. ከዚያ በኋላ በተለያየ ጊዜ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን፣ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ እንዲሁም ከምግብ ዋስትና ቢሮ ጋር በማዋሃድ የአደጋ መከላከል ዝግጁነትና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ሆኖ በግብርና ሚኒስቴር ስር ተዋቅሮ በሚኒስቴር ዲኤታ የሚመራ ተቋም ሆኖ ነበር፤ ከዚያ በደንብ ቁጥር 363/2008 ብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን በሚል ተቋቁሟል፡፡
5. በ2014 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ እና የስትራቴጂክ ለመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደርን በማዋሃድ የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በመባል ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እንዲሆን ተወስኖ እንደ አዲስ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

## የኮሚሽኑ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴት፣ ዓላማ፣ ስልጣንና ተግባር

### ራዕይ

6. በ2030 ዓ.ም ለአደጋ ስጋት የማይበገር ህዝብና ሀገር ተገንብቶ ማየት፡፡

### ተልዕኮ

7. ዘመናዊ ፣ የተቀናጀ፣ ተጠያቂነትን ያማከለ፣ ቀድሞ ተንባይና ተግባሪ (Anticipatory & Proactive) ፣ ቀልጣፋ ምላሽ ሰጪ (Responsive) ፣ ማህበረሰብ ተኮር ፣ ዘርፈ-ብዙ የአደጋ መንስኤና ተዋናዮችን መሰረት ያደረገ እንዲሁም ብሔራዊ የደህንነት እሳቤዎችን ያካተተ የአደጋ ስጋት ቅነሳና ምላሽ አሰጣጥ ስራ አመራር ስርዓት መዘርጋት እና ውጤታማ ማድረግ ነው፡፡

## የኮሚሽኑ ዓላማ

8. የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 363/2008 መሰረት ለኮሚሽኑ የተሰጡ ዓላማዎች፡-

- ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ በተሟላ መልኩ እንዲተገበርና ዓላማዎቹ እንዲሳኩ ለማስቻል አግባብ ያላቸውን ተግባራት ማከናወን፣
- በመሪ ሴክተር መ/ቤቶች የሚከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ የማስተባበር፣ ክትትል ማድረግና ተገቢውን ድጋፍ መስጠት

ናቸው፡፡

## የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር

9. ኮሚሽኑ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 363/2008 ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መካከል፡-

- የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በመንግስት የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የልማት ዕቅድና ፕሮግራሞች፣ በግል መ/ቤቶች ዕቅዶች እንዲሁም በስርዓተ-ትምህርት መካተቱን ያረጋግጣል፤ ከዚህ ጋር በተያያዘም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ያደርጋል፣
- በአደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነድ ላይ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች ተብለው የተሰየሙ የፌደራል መንግስት የአስፈፃሚ አካላት በዕቅዳቸው ውስጥ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ማካተታቸውን ያረጋግጣል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

- በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ የትግበራ ዕቅዶችን አሰባስቦ ያደራጃል፣ አፈፃፀሙን በየጊዜው ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር ምክር ቤት ስራ አፈፃፀሙን ቢያንስ በበጀት አመቱ ሁለት ጊዜ ሪፖርት ያቀርባል፤
- የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ምላሽ እና የአደጋ ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
- ማንኛውንም መሪ ሴክተር መስሪያ ቤትን የማይመለከት ወይም ከመሪ ሴክተር መ/ቤት አቅም በላይ የሆነ ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥም የምላሽ ስራውን ይሰራል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፤
- ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ክምችት ይይዛል፣ ያስተዳድራል፤
- አስቸኳይ ጊዜ የዕለት ምግብ ዕርዳታ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ስትራቴጂክ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችትን ከሚያስተዳድር የሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት የዕርዳታ እህል በመውሰድ የዕርዳታ እህል ያሰራጫል፤
- ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ዝግጅትና ክለሳ ስራን ይመራል፣ ያስተባብራል፤
- የአደጋ ስጋት ፕሮፋይልን መሰረት በማድረግ የተሟላ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት በየደረጃው ይዘረጋል፣ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ የተዘረጋው ስርዓት ተደራሽ፣ ለአደጋ ምላሽ ሰጪና ዝግጁ እንዲሁም ለድንገተኛ ደራሽ አደጋዎች የታቀዱ ዕቅዶች ተግባራዊ መሆን መቻላቸውን ለማረጋገጥ በየደረጃው በተከታታይ ወይም በዕቅድ ላይ ተመስርቶ የናሙና ልምምዶች እንዲከናወኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የማስተካከያ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤
- በቅድመ-አደጋ፣ በአደጋና በድህረ-አደጋ ወቅት የአደጋ ስጋት ትንበያን ጨምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ጥናቶችንና ግምገማዎችን ይመራል፣ ያስተባብራል፤
- የፌደራል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን ስራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ ይመራል፣ ያስተዳድራል፤ እንዳስፈላጊነቱም ተመሳሳይ ማዕከል በፌደራል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ መስተዳድሮች በሚገኙ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች እንዲመሰረት ድጋፍ ያደርጋል፤
- የመረጃና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤ በብሄራዊ ደረጃ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣ እንዳስፈላጊነቱ የክልል መስተዳድሮች ተመሳሳይ የመረጃ ማዕከል እንዲያቋቁሙ ድጋፍ ያደርጋል፤

- አደጋ በይፋ መገለፁን ተከተል የአደጋ ስራ አመራር ም/ቤት ሲወስን ከአገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ሀብት ያሰባስባል፤
- የተገኘውን ሀብት በራሱና በሌሎች የሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መስተዳድሮች በሚገኙ መሪ የሴክተር መ/ቤቶች አማካኝነት ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ስራ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ስርዓት በፍላጎት በተደራጁና በውጤት ላይ የተመሰረተ የአደጋ ስጋት ስራዎችን በሚሰሩና በበጎ ፈቃደኞች የሚታገዝበትን አሰራር ይዘረጋል፤ በተሟላ መልኩ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
- አግባብነት ባላቸው የአገሪቱ ህጎች መሰረት ለብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ትግበራ አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር አግባብነት ካላቸው ዓለም አቀፍ፣ ድርጅቶች እና የመንግስትና የግል መ/ቤቶች ጋር የስራ ግንኙነት ይፈጥራል፣ ይተባበራል፣ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## የኮሚሽኑ አደረጃጀትና የሰው ኃይል

### የኮሚሽኑ አደረጃጀት

10. የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚንስትሩ ሆኖ በአንድ ኮሚሽነር እና በሶስት ም/ኮሚሽነር የሚመራ ሲሆን በኮሚሽኑ ስር አንድ ጽ/ቤት እና በስሩ አምስት ስራ አስፈፃሚ ፣አንድ ማስተባበሪያ ማዕከል እና በስሩ አምስት ስራ አስፈፃሚ እንዲሁም ዋና ስራ አስፈፃሚ ስር ስድስት ስራ አስፈፃሚ ያሉ ሲሆን በሶስቱ ም/ኮሚሽነሮች ስር አስራ አንድ ስራ አስፈፃሚዎች እንዲኖሩ ተደርጎ ተዋቅሯል፡፡ የኮሚሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር የሚያሳይ መረጃ በአባሪ አንድ ተያይዟል፡፡

### የሰው ኃይል

11. ኮሚሽኑ እስከ ጥር 2017 ዓ.ም 537 ሴት እና 564 ወንድ በድምሩ 1101 ቋሚ እና ጊዜያዊ ሰራተኞች ያሉት ሲሆን እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ተቀምጧል፡፡

| አሁን፡ያለው የሠራተኛ/ባለሙያ ብዛት | ቋሚ | | ጊዜያዊ/ኮንትራ | | ማስተርስና ከዛ በላይ | | ዲግሪ | | ዲፕሎማ | | ከ12ኛ ወይም ከ10ኛ ክፍል በታች | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| | 527 | 535 | 10 | 29 | 14 | 42 | 82 | 112 | 182 | 82 | 251 | 299 | 537 | 564 |
| ድምር | 1062 | | 39 | | 56 | | 194 | | 264 | | 550 | | 1101 | |

## የኮሚሽኑ የፋይናንስ ምንጭ

12. የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት መደበኛ እና ካፒታል በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2013-2016 ዓ.ም ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

መደበኛ በጀት እና አፈፃፀም

| በጀት ዓመት | የተበጀተ በጀት በብር | ስራ ላይ የዋለ | ስራ ላይ ያልዋለ | አፈፃፀም በመቶኛ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2013 | 18,223,950,973.50 | 17,835,635,726.93 | 388,315,246.57 | 97.8% | |
| 2014 | 20,778,738,235.70 | 20,660,606,497.70 | 118,131,738.00 | 99.4% | |
| 2015 | 23,623,848,857.00 | 20,810,503,296.92 | 2,813,345,560.08 | 88.1% | |
| 2016 | 12,951,746,114.74 | 12,928,037,114.73 | 23,709,000.01 | 99.8% | |
| 2017* | 10,400,000,000.00 | 6,129,673,899.55 | 4,270,326,100.45 | 59% | |

*የስድስት ወር አፈጻጸም

ካፒታል በጀት እና አፈፃፀም

| በጀት አመት | የተበጀተ በጀት በብር | ስራ ላይ የዋለ | ስራ ላይ ያልዋለ | ሥራ ላይ ያልዋለው በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2013 | 541,849,000.00 | 182,375,049.47 | 359,473,950.53 | 66% | |
| 2014 | 280,432,710.45 | 178,750,647.11 | 101,682,063.34 | 36% | |
| 2015 | 840,000,000.00 | 154,436,273.90 | 685,563,726.10 | 82% | |
| 2016 | 812,962,645.00 | 812,962,645.00 | ----- | 0% | |
| 2017* | 1,500,000,000.00 | 874,377,820.84 | 625,622,179.16 | 58.3% | |

<u>ማብራሪያ፡-</u>ብር 23,709,000.01 ስራ ላይ ያልዋለው ከገንዘብ ሚንስቴር በጀቱ ተጠይቆ ባለመለቀቁ ነው፡፡
- *የ2017 በጀት አፈፃፀም የሚያሳየው እስከ ሁለተኛው ሩብ ዓመት ያለውን ነው፡፡

## የኮሚሽኑ ሰብዓዊ እርዳታ/ድጋፍ/ ሥርጭት አተገባበር የስራ ፍሰት

- ❖ ዕለት ደራሽ የምግብ ድጋፍ አቅርቦት ወይም ምላሽ የሚሰጠው በዓመት ሁለት ጊዜ ይፋ በሚደረገው የሰብዓዊ እርዳታ ፍላጎት ሠነድ መሰረት በፌደራል መንግስትና አጋር አካላት ቅንጅትና ትብብር አማካኝነት በሚደረግ ጥናትና ጥናቱ በሚያሳየው ውጤት ተመስርቶ ነው፡፡
- ❖ የሰብዓዊ እርዳታ ጥያቄ አቀራረብ ክልሎች የተደረገውን ጥናት ተከትለው በጥናቱ በተገኘው ውጤት መሰረት የሰብዓዊ እርዳታ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ወገኖች የፍላት ጥያቄ በዞን፣ በወረዳ፣ በማራገፊያ ጣቢያ እና በተጠቃሚ ቁጥር በመለየት በደብዳቤ ለኮሚሽኑ ይልካሉ /ያቀርባሉ/
- ❖ ከክልሎች የቀረበው /የተላከው/ ጥያቄ ለኮሚሽኑ የአደጋ ስጋ ቅነሳ ዘርፍ ይቀርባል፡ ፡

- በዘርፉ በኩል በክልሉ የቀረበው የድጋፍ ጥያቄ በመረጃና በማስረጃ ተረጋግጦ እንዲቀርብ (verification) ወደ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት ይመራል፡፡
- የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት የክልሎቹን ጥያቄ ከተገኘው የጥናት ውጤት ጋር በማመሳከር የሰብዓዊ ድጋፍ እንዲሰጥና እንዲላክ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡
- በተሰጠው የውሳኔ አስተያየት መሰረት የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዘርፍ ለስትራቴጂክ ሎጀስቲክ ስራ አመራር ዘርፍ ለአስፈላጊው አፈፃፀም ይመራል፡፡
- የስትራቴጂክ ሎጀስቲክ ስራ አመራር ዘርፍ ለስትራቴጀክ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ክምችት አስተዳደር (ለስ/ም/ም/ያ/ክ/አ) ዳይሬክቶሬት እና ለሎጀስቲክ ኦፕሬሽን ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ለአስፈላጊው አፈፃፀም ይመራሉ፡፡
- የሎጀስቲክ ኦፕሬሽን ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት የዕርዳታ /የሰብአዊ ድጋፍ/ መጠየቂያ በመሙላትና የድጋፍ ድልድል ሬሽን በማዘጋጀት ለስ/ም/ም/ያ/ክ/አ/ ዳይሬክቶሬት ይልካል፡፡
- የስ/ም/ም/ያ/ክ/አ/ ዳይሬክቶሬት እንደቦታው ቅርበትና እንደ ክምችቱ አቅም ሰብዓዊ ድጋፍ ወጪ የሚሆንበት መጋዘን ድልድል ይሰራል፡፡
- የሎጀስቲክ ኦፕሬሽን ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በተሰጠው የመጋዘን ድልድል መሰረት ለቦታዎቹ በጨረታ ላለፉት ድርጅቶች የትራንስፖርት ኦርደር አዘጋጅቶ ከአጓጓዥ ድርጅቶች ጋር በመፈራረም ለቅ/ጽ/ቤቶች ይልካል፡፡
- የስ/ም/ም/ያ/ክ/አ/ ዳይሬክቶሬት የእርዳታ ስርጭት መጠየቂያዎቹ ለየቅ/ጽ/ቤት ይልካል፡፡
- ቅ/ጽ/ቤቶች በተላከላቸው የእርዳታ ስርጭት መጠየቂያ እና ትራንስፖርት ኦርደር መሰረት ለቦታዎቹ ያለፉት አጓጓዥ ድርጅቶች በሚያቀርቧቸው ተሽከርካሪዎች የሰብዓዊ ድጋፉን በሰነድ ያስረክባሉ፡፡
- ድጋፉን የሚያጓጉዙ ትራንስፖርተሮች ድጋፉን ክልሎች እንዲራገፍላቸው ለጠየቁት ማራገፊያ ቦታ ድረስ በመውሰድ በሰነድ ያስረክባሉ ክልሎች የደረሳቸውን እርዳታ ተረክበው በአግባቡ በመጠበቅ/በመያዝ ባላቸው አሰራር መሰረት ዕርዳታው ለተጠየቀላቸው ወገኖች የማሰራጨትና የማከፋፈል ስራ ዋና ሃላፊነት የእነሱ በመሆኑ በዚሁ መሰረት ያከናውናሉ፡፡
- ትራንስፖርተሮች የሰብዓዊ ድጋፍ ላጓጓዙበት ከማራገፊያ ጣቢያ የገቢ ማረጋገጫ ሰነድ ይረከባሉ፡፡

- አጓጓዥ ድርጅቶች ወጪ ያደረጉበትን የወጪ እንዲሁም ገቢ ያደረጉበትን የገቢ ሠነዶችን፣ የጭነት ማዘዣዎችን፣ ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎችን በማያያዝ የማጓጓዣ የክፍያ ጥያቄያቸውን የሎጀስቲክ ኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባሉ፡፡
- የቀረቡ ሰነዶች ተጣርተውና ትክክለኛነታቸው ተረጋግጦ ለክፍያ ለፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ይላካል፡፡ በዛም በኩል ተገቢው ማጣራት ተደርጎ ለአጓጓዦች ክፍያ እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ፡-

13. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የኮሚሽኑ የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ችግሮች ወይም ክፍተቶች ካሉ ችግሮቹን እና መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን  ለማቅረብ ነው፡፡

## የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

### የኦዲት ወሰን

14. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ሲሆን በኢትዮጵያ የክዋኔ የኦዲት ስታንዳርድ እንዲሁም ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2014 ዓ.ም እስከ 2017 2ኛ ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ያለውን የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት አፈፃፀምን በተመለከተ በኮሚሽኑ የተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎችን ይሸፍናል፡፡

### የኦዲት ዘዴ

15. ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት በኮሚሽኑ የተከናወነ ሲሆን በኮሚሽኑ ካሉ 8 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች (ማዕከላዊ መጋዘኖች) መካከል በሶስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች (ማዕከላዊ መጋዘኖች)፣ በሚመለከታቸው የክልል አደጋ ስጋት ቢሮዎች እንዲሁም በተመረጡ መጠለያ ጣቢያዎች በአካል በመገኘት እና መጠይቅ በማቅረብ ቼክሊስት በመሙላት እና ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመከለስ በተጨማሪም ለክልል አደጋ ስጋት አመራር ቢሮዎች በኢሜል መጠይቅ በመላክና ተጠይቀው የቀረቡ ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመሰብሰብና በመከለስ ነው፡፡ መጠይቅ የተላከላቸው የክልል አደጋ ስጋት አመራር ቢሮዎች ለትግራይ ብ/ክ/መ/፣ ለአፋር ብ/ክ/መ/፣ ለአማራ ብ/ክ/መ/፣ ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/፣ለጋምቤላ ብ/ክ/መ/፣ ለደቡብ ኢትዮጵያ ህ/ክ/መ፣ ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ህ/ብ/ክ/መ/፣ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህ/ክ/መ/፣ እና ለሲዳማ ብ/ክ/መ/ መጠይቅ የተላከላቸው ሲሆን መጠይቁን ሞልተው የላኩት ክልሎች ግን የጋምቤላ ህ/ብ/ክ/መ/አደጋ

ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህ/ክ/መ/አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ቢሮዎች ብቻ ናቸው፡፡

16. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የመስክ ጉብኝት የተደረገባቸው እና በኢሜል መጠይቅ የቀረበላቸው የክልል አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ጽ/ቤቶች እንዲሁም መጠለያ ጣቢያዎች ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)

17. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ "በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው ፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች

18. ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) የኦዲቱን ዓላማ ለማሳካት በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን እና በስሩ የሚገኙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች/ማእከላዊ መጋዘኖች/ "የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት ውጤታማነትን በተመለከተ ለመገምገም ሶስት ዋና ዋና የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) የተለዩ ሲሆን እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም፡-

- ☞ ኮሚሽኑ ሰብዓዊ ዕርዳታ ለማቅረብ የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም
- ☞ ኮሚሽኑ በሌሎች አጋር አካላት የሚከናወኑ የሰብዓዊ ዕርዳታ ተግባራትን ለማስተባበር፣ ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም
- ☞ ኮሚሽኑ የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦትና ስርጭት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበትንና መረጃ የሚለዋወጥበትን የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም የሚሉት ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

19. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ ሐያ ሰባት (27) የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የተከለሱ ሰነዶች በአባሪ 4 ተያይዟል፡፡የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ተልከው የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡባቸው

በማድረግ በኦዲት መመዘኛዎቹ ላይ ስምምነታቸውን ገልፀዋል፡፡ (የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ 2 ተያይዘዋል)

# ክፍል ሁለት


## የኦዲት ግኝቶች

### ለመጠለያ ጣቢያዎች (ተፈናቃዮች) የሚላከው የእርዳታ እህልና ቁሳቁስ የሰብዓዊ እርዳታ ፈላጊ ቁጥርን ያገናዘበ መሆኑን በተመለከተ፡፡

20. ኮሚሽኑ ለክልሎች የሚላከው የእርዳታ እህልና ቁሳቁስ በተጠናው የሰብዓዊ እርዳታ ፈላጊ ቁጥርና በቀረበው ፍላጎት መሰረት የሰብዓዊ እርዳታ እህልና ቁሳቁስ መድረሱንና ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ክትትል በማድረግ የድጋፍና የቁጥጥር ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡


21. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረባቸው ቃለ መጠይቅ፡-


- ❖ በኮሚሽኑ ከሚያዝያ እስከ ግንቦት 2016 ዓ.ም (Apr.-may. 2024) Round 35 & 36 በተደረገ የተረጂዎች ልየታ ጥናት መሰረት ወደ 2738 የሚጠጋ መጠለያ ጣቢያዎች የነበሩ ሲሆን ከፍተኛ መጠለያ ጣቢያዎች የነበሩት በሱማሌ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይና በአማራ ክልል መሆኑ ከኮሚሽኑ በሶፍት ኮፒ ከቀረበ ማስረጃ መታወቁ፣



❖ በኮሚሽኑ ከሚያዝያ እስከ ግንቦት 2016 ዓ.ም (Apr.-may. 2024) Round 35 & 36 በተደረገ የተረጂዎች ልየታ ጥናት መሰረት በሁሉም ክልሎች የነበሩ የውስጥ ተፈናቃዮች ብዛት 3,306,698 የነበረ መሆኑን ከኮሚሽኑ በሶፍት ኮፒ ከቀረበ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

(የተፈናቃዮች ብዛት በክልል፣ በዕድሜ እና በጾታ ከታች ያለውን ቻርት ሠንጠረዥ በአባሪ 5.ተያይዟል)




| | ዕድሜ ከ 0-4 | ዕድሜ ከ5-14 | ዕድሜ ከ 15-17 | ዕድሜ ከ 18-59 | ዕድሜ ከ 60+ |
|---|---|---|---|---|---|
| ወንድ | 245588 | 528695 | 80613 | 671915 | 54875 |
| ሴት | 243702 | 586682 | 89892 | 764807 | 39929 |
| ድምር | 489290 | 1115377 | 170505 | 1436722 | 94804 |

ነገር ግን አልሚ ምግብ (CSB) እና እህል መቅረብ ሲገባው በቂ የሰብአዊ ዕርዳታ እየቀረበላቸው አለመሆኑን በመስክ ምልከታና በሰነድ ክለሳ ለማወቅ ተችሏል፡፡

22. ስለጉዳዩ ለኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ከአልሚ ምግብ ጋር ተያይዞ ለተነሳው ጥያቄ እንደማሳያ ኮሚሽኑ በ2016/2017 ዓ.ም የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ከጥር ወር 2016 እስከ ህዳር ወር 2017 ዓ.ም ድረስ በተደረገ የስብአዊ ድጋፍ አቅርቦት 103,313 ኩንታል አልሚ ምግብ ማሰራጨት መቻሉን እና ክልሎች በሚያቀርቡት የተረጂዎች ቁጥር መሠረት ኮሚሽኑ አስፈላጊ ማጥራቶችን ካደረገ በኋላ ለክልሎች የሰብዓዊ ዕርዳታ እንደሚያቀርብና ዕርዳታውም በመመሪያው መሰረት ህጻናት፣ ነብሰጡር እናቶችና አቅመ ደካሞች የቅድሚያ ቅድሚያ እንዲያገኙ እየተደረገ መሆኑን ልፀዋል፡፡

23. የኮሚሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ አልሚ ምግብ (CSB) በተመለከተ ከጥር ወር 2016 እስከ ህዳር ወር 2017 ዓ.ም ድረስ በተደረገ የስብአዊ ድጋፍ አቅርቦት 103,313 ኩንታል አልሚ ምግብ ማሰራጨት መቻሉን የተገለፀ ቢሆንም ለኦዲት ቡድኑ በቀረበው ማስረጃ መሰረት ግን በርካታ አካባቢዎች ማለትም በአፋር፣ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች የተመደበው እርዳታ ያልተሰራጨ (dispatch) ያልተደረገ እና ተመድቦ ያልተሰራጨው እርዳታ ምን እንደተደረገ ማብራሪያ ያልተሰጠበት በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

24. በመሆኑም እርዳታ በወቅቱ በሁሉም መጠለያዎች ለሚገኙ ተፈናቃዮች በተለይም ለህጻናት እንዲደርስ ካልተደረገ ተፈናቃዮቹን ለተጨማሪ ጉዳትና እንግልት እንዲዳረጉ ያደርጋል፡፡

**ኮሚሽኑ የሰብዓዊ ዕርዳታ ሲያሰራጭ አጥቢ፣ ነብሰ ጡር እናቶችና ህፃናት የተመጣጠነ ምግብ ማግኘታቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑን በተመለከተ፡፡**


25. ኮሚሽኑ የሰብዓዊ ዕርዳታ ሲያሰራጭ የአጥቢ፣ ነብሰ ጡር እናቶችና ህፃናት ፍላጎቶችን ያገናዘበ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

26. በፌደራልና ክልል መንግስታት በጋራ በተዘጋጀው የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ እርዳታ ቁሳቁሶች አስተዳደር ማንዋል (የሰብዓዊ የዕለት ዕርዳታ እና የልማታዊ

ሴፍቲኔት ፕሮግራም) ላይ የተጨማሪ አልሚ ምግብ (በቆሎና አኩሪ አተር ቅይጥ (CSB) ከአምስት አመት በታች ለሆኑ ህፃናትና ለነፍሰጡር ወይም ለሚያጠቡ እናቶች ከመደበኛው የእርዳታ ምግብ በተጨማሪ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ይገልፃል፡፡

27. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረባቸው ቃለ መጠይቅ፡- ፡-

- በኮሚሽኑ ከሚያዝያ እስከ ግንቦት 2016 ዓ.ም (Apr.-may. 2024) Round 35 & 36 በተደረገ የተረጂዎች ልየታ ጥናት መሰረት በሃገሪቱ የሚገኙ ከአምስት ዓመት በታች ተረጂ ህፃናት ቁጥር 489,290 (15%) የሚገኙ ቢሆንም የሰብዓዊ እርዳታው በተለይ አልሚ ምግብ (CSB) ለየክልሎቹ የተመደበ (allocated) የተደረገ ስለመሆኑ በሶፍት ኮፒ ከቀረበው የስርጭት መረጃ ለማወቅ ቢቻልም በርካታ አካባቢዎች (በአፋር፣ በአማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች) የተመደበው እርዳታ ያልተሰራጨ (dispatch) ያልተደረገ መሆኑ፣




| | አፋር | አማራ | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጋምቤላ | ሐረሪ | ኦሮሚያ | ሲዳማ | ሶማሌ | ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ትግራይ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወንድ | 6415 | 8951 | 4779 | 2261 | 3054 | 121 | 65917 | 2850 | 110039 | 460 | 40741 | 245588 |
| ሴት | 6636 | 8521 | 5303 | 2319 | 3223 | 90 | 75221 | 2862 | 97775 | 495 | 41257 | 243702 |
| ድምር | 13051 | 17472 | 10082 | 4580 | 6277 | 211 | 141138 | 5712 | 207814 | 955 | 81998 | 489290 |

- ዕድሜያቸው ከ0-4 የሆኑ ተፈናቃይ ህጻናት ብዛት በክልል የሚገኙትን (በአባሪ 6 ተያይዟል)

- በፌደራልና ክልል መንግስታት በጋራ በተዘጋጀው የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ እርዳታ ቁሳቁሶች አስተዳደር ማንዋል (የሰብዓዊ የዕለት ዕርዳታ እና የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም) ላይ ያለተጨማሪ መስፈርት በምንም አይነት መልኩ ተጨማሪ

አልሚ ምግብ ለሁሉም ተረጂዎች/ተጠቃሚዎች በጅምላ መከፋፈል እንደሌለበት ቢገልፅም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ መጠለያ ጣቢያዎች መካከል በሐረር ከተማ በሚገኘው ሐማሬሳ መጠለያ ጣቢያ የተጨማሪ አልሚ ምግብ (በቆሎና አኩሪ አተር ቅይጥ CSB (corn, soya & bean) ይቀርብ በነበረበት ጊዜ ከአምስት አመት በታች ያሉ ህፃናት ብዛት 91፣ አጥቢ እናቶች ብዛት 26 እና ነፍሰጡር እናቶች ብዛት 15 ሲሆኑ በአጠቃላይ ለ132 ተጠቃሚዎች ብቻ መሰጠት የሚገባው ቢሆንም ለሁሉም ተረጂዎች ያለ ምንም ተጨማሪ መስፈርት ይሰጥ (ይከፋፈል) እንደነበር ለሐረሪ ክልል አደጋ ስጋት ቢሮ ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ መጠለያ ጣቢያዎች በሐረር (ሐማሬሳ) ፣ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን በካራሚሌ ከተማ ጎሮ ጉቱ ወረዳ የሚገኙ አራት መጠለያ ጣቢያዎች (ጊጊዴ፣ አልሼኮ፣ ግብርና እና ገንደ ወጋየሁ) እንዲሁም በዚሁ ዞን በደደር ወረዳ የሚገኙት ስድስት መጠለያ ጣቢያዎች (ጊው ጎልማሳ፣ ኦልድ ጎልማሳ፣ ኢ.ዲ.ዲ.ሲ.፣ የወጣቶች ማዕከል፣ ውሃ ቢሮ እና ቄይራ) የተሰኙ መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚገኙ ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት፣ ነብሰጡር እና አጥቢ እናቶች የተጨማሪ አልሚ ምግብ (CSB) ካገኙ ወይም ከተቋረጠባቸው ከሁለት ዓመት በላይ መሆኑ

በመስክ ምልከታና ከሰነድ ክለሳ ለማወቅ ተችሏል፡፡

28. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ኮሚሽኑ

- የሰብዓዊ ዕርዳታ ሲያሰራጭ አጥቢ፣ ነብሰ ጡር እናቶችና ህፃናት የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ በፌደራልና ክልል መንግስታት በጋራ በተዘጋጀው የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ እርዳታ ቁሳቁሶች አስተዳደር ማንዋል መሠረት በአስቸኳይ አደጋ ጊዜ ለሁሉም እንደሚሰጥ የልየታ መመሪያው /Targeting guide line/ የሚያዝ መሆኑ፣

- በተጨማሪም አንዳንድ ግዜ የተሟላ ጥራጥሬ በማይቀርብበት ጊዜ CSB ክፍተቱን ለመሸፈን ለተረጅዎች ለሁሉም እንዲሰጥ እንደሚደረግ፣ National Guidelines on targeting Relief Food Assistance 2011 የጠቀሱ ሲሆን

* ለግለሰብ (ተረጂው) ጋር እርዳታውን የማድረስ ሥራውን በየደረጃው ከክልል ጀምሮ ባለው መንግስታዊ መዋቅር በኩል የሚፈጸም ሆኖ ኮሚሽኑ ለዚሁ ሥራ ባዋቀረው የስራ ክፍል በኩል የኢንስፔክሽን ሥራ እየሰራ እንደሚገኝ፣ ችግሮችንም በዚሁ አግባብ እየፈታ እንደሆነ፣
* በቀጣይም በዚሁ መልክ የክትትልና ቁጥጥር ሥራው እንደሚሰራ እንዲሁም ያለ አግባብ ሳይሰራጩ የሚከማቹ ወይም ያለ አግባብ ከታለመላቸው አካላት ውጪ የተሰራጨ ምግብና ምግብ ያልሆነ ድጋፎችን በመለየት ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የእርምት እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን

ገልፀዋል::

29. የኮሚሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ በፌደራልና ክልል መንግስታት በጋራ በተዘጋጀው የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ እርዳታ ቁሳቁሶች አስተዳደር ማንዋል መሠረት በግልፅ እንደተቀመጠው ያለተጨማሪ መስፈርት በምንም አይነት መልኩ ተጨማሪ አልሚ ምግብ ለሁሉም ተረጂዎች/ተጠቃሚዎች በጅምላ መከፋፈል እንደሌለበት የሚገልፅ በመሆኑ በተጨማሪም የተሟላ ጥራጥሬ በማይቀርብበት ጊዜ CSB ክፍተቱን ለመሸፈን ለተረጅዎች ለሁሉም እንዲሰጥ ይደረጋል በማለት በኃላፊዎች የተገለፀ ቢሆንም ለህፃናት የሚከፋፈለው አልሚ ምግብን (CSB) በፍጥነት ስለማይላክ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

30. በመሆኑም ለህፃናት፣ ለአጥቢና ነፍሰጡር እናቶች ተብሎ የሚላክ አልሚ ምግብ (CSB) ያለ ተጨማሪ መስፈርት ለተረጂዎች የሚከፋፈል ከሆነ እንዲሁም ለሌሎች እንዲከፋፈል የተደረገው በአፋጣኝ ካልተተካ በዋነኛነት አልሚ ምግብ የሚያስፈልጋቸው አካላት ላይ ዕጥረት በመፍጠር ህፃናት፣ አጥቢና ነፍሰጡር እናቶች ለከፍተኛ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡

**በመጠለያ ጣቢያዎች መሠረታዊ መሰረተ ልማት መሟላታቸውን በተመለከተ**

**ኮሚሽኑ በሃገሪቱ በሚገኙ በሁሉም መጠለያ ጣቢያዎች መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡**

31. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረባቸው ቃለ መጠይቅ፡-

❖ የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ ተረጂዎች የሚያስፈልጋቸው የህክምና አገልግሎት በተገቢው ሁኔታ ለሁሉም እንዲዳረስ

ያልተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪም በደደር በሚገኙ ስድስት መጠለያ ጣቢያዎች ምንም አይነት ህክምና የማያገኙ መሆኑ፣

❖ የኦዲት ቡድኑም የመስክ ምልከታ ባደረገባቸው በሶማሌ ክልል በሚገኘው ቆሎጂ መጠለያ ጣቢያ ፣ በሐረሪ ክልል በሚገኘው ሐማሬሳ መጠለያ ጣቢያ፣ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን በካራሚሌ ከተማ የሚገኙት አራት መጠለያ ጣቢያዎች (ኒጊዴ፣ አልሼኮ፣ ግብርና እና ገንደ ወጋየሁ) እንዲሁም በዚሁ ዞን በደደር ወረዳ የሚገኙት ስድስት መጠለያ ጣቢያዎች (ኒው ጎልማሳ፣ ኦልድ ጎልማሳ፣ ኢ.ዲ.ዲ.ሲ.፣ የወጣቶች ማዕከል፣ ውሃ ቢሮ እና ቄይራ) መጠለያ ጣቢያዎች ውሃ መብራትና የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት ለረጅም ጊዜ የተቋረጠ መሆኑ፤ (አገልግሎት የማይሰጡት የዉሃ ታንከር እና የመጸዳጃ ቤቶች በሚቀጥለዉ ስእላዊ መግለጫ ቀርበዋል)



ፎቶ ቁ.1. በኦሮሚያ ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሮ ጉቱ እና ደደር ወረዳ በሚገኙት መጠለያ ጣቢያዎች የውሃ ቦኖና ታንከር አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑን የሚያሳዩ



ፎቶ ቁ.2. ሐረር (ሐማሬሳ) የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያ በውሃ እጦት ምክንያት ህንፃው ለብልሽት የተጋለጠና ሽንት ቤቶቹም በብልሽት አገልግሎት የማይሰጡ መሆናቸውን የሚያሳይ



ፎቶ ቁ.3.በሶማሌ ክልል ባቢሌ አካባቢ የሚገኘው ቆሎጂ መጠለያ ጣቢያ የተፈናቃዮች መፀዳጃ ቤት ከሌሎቹ መጠለያ ጣቢያዎች ሲነጻጸር የተሻለ መጸዳጃ ቤት የተገነባ መሆኑን የሚያሳይ



ፎቶ ቁ.4. በኦሮሚያ ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ደደር ወረዳ ኦልድ ጎልማሳ መጠለያ ጣቢያ የሚገኘው መጸዳጃ ቤት ተበላሽቶ አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑን የሚያሳይ

32. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ

- ❖ ህክምናና የመድኃኒት አቅርቦትን በተመለከተ በዋናነት የሚመለከተው ጤና ሚኒስቴር መሆኑንና፤
- ❖ በአሠራር የጤና አገልግሎት የሚፈልጉ ወገኖች የአገልግሎት ሽፋኑን የሚያገኙት ተፈናቃዮቹ በሚገኙበት አካባቢ ከሚገኝ የጤና ጣቢያ ወይንም የጤና ኬላ እንደ አስፈላጊነቱም በሪፈራል ስርዓት በክልሉ ወይንም ከክልሉ ወጪ በሚገኙ ሆስፒታሎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ስርዓት የሚከተል መሆኑን፣
  - ❖ በሐማሬሳ ያሉ ተፈናቃዮች ለረጅም ጊዜ በመጠለያ ጣቢያው ከማህበረሰቡ ጋር የቆዩና በማህበረሰብ ውስጥ በመሆናቸው ምክንያት አሁን የተፈጠረው ችግር

የሚፈታው እንደማንኛውም ማህበረሰብ የልማት ሥራ በሚሰራበት ወቅት በአካባቢው የመንግስት መዋቅር የሚሰራ እንደሆነ፣

- ❖ በትንሹ እነዚህ ተፈናቃዮች ከስምንት ዓመት በላይ ከማህበረሰቡ ጋር የኖሩ በመሆናቸው አስቸኳይ ተፈናቃይ የሚለውን መስፈርት የማያሟሉ መሆናቸው ምላሹም የሚሰጠው ልክ ችግሩ ባለብዙ ዘርፉ እንደመሆኑ መጠን መፍትሄውንም የሚሰጡት የተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶችም ጭምር በመሆናቸው በቀጣይ የሚሰራ መሆኑን፣
- ❖ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን የመጠለያ ጣቢያዎችን የሚያስተዳድሩት በየአካባቢው ያለው መዋቅር በመሆኑ በነሱ በኩል የቅርብ ክትትል እንዲደረግ ይሰራል በማለት

ገልፀዋል፡፡

33. የኮሚሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡-የኦዲት ቡድኑ የመስክ ምልከታ ባደረገባቸው መጠለያ ጣቢያዎች በተለይ በሶማሌ ክልል በሚገኘው ቆሎጂ መጠለያ ጣቢያ የተሻለ መፀዳጃ ቤት የተሰራ ቢሆንም በሌሎቹ መጠለያ ጣቢያዎች መሰረታዊ መሰረተ ልማቶች ማለትም ውሃ፣ መጸዳጃ ቤት፣ መጠለያ ጣቢያ ፣ እና መብራት ለሁሉም መጠለያ ጣቢያዎች ያልተሟላ በመሆኑ እና በአካባቢው ያለው አስተዳደር ትኩረት ያልሰጣቸው በመሆኑ እና በየመጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ መጸዳጃ ቤቶችን በተመለከተ የተባለ ነገር ባለመኖሩ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

34. በመሆኑም ኮሚሽኑ አስፈላጊው መሰረተ ልማት በሁሉም መጠለያ ጣቢያዎች እንዲሟሉ ካላደረገ ተፈናቃይ ወገኖች ለተለያዩ በሽታዎች የተጋለጡ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

## በኮሚሽኑ አስፈላጊ የሆኑ የትራንስፖርት እና የሎጅስቲክስ አቅርቦት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፡፡

35. ኮሚሽኑ ለከፍተኛና ለዘርፈ-ብዙ አደጋዎች ሲከሰቱ አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑ ሎጅስቲክስ/ በአፋጣኝ ለዕርዳታ ፈላጊዎች የሚደርስበት የትራንስፖርት አቅርቦት ጨምሮ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ስርዓት በመዘርጋት ሊተገበር ይገባል፡፡

36. በኮሚሽኑ የ10 ዓመት (2013-2022) መሪ ዕቅድ ገፅ 106 ላይ ለቅድመ ማስጠንቀቂያና አስቸጋሪ በሆነ ሥፍራ ላይ አደጋ የደረሰባቸውን ለፈልጎ ማዳን የሚያግዙ ሎጀስቲኮችን ለማሟላት በዕቅድ የተያዘ መሆኑን ይገልፃል፡፡

37. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረባቸው ቃለ መጠይቅ፡- ለከፍተኛና ለዘርፈ-ብዙ አደጋዎች አስፈላጊ የሆኑ ሎጀስቲክስ/ ሄሊኮፕተር፣ ማሽነሪዎች (ዶዘር፣ ኤክስካቫተር)፣ ጀልባዎች፣ ወዘተ የመሳሰሉ መሳሪያዎች በኮሚሽኑ እንዲሁም በክልል አደጋ ስጋት አመራር ቢሮዎች የማይገኙ መሆኑ፣ ወይንም ሲያስፈልጉ ከሌሎች አካላት በውሰትም ሆነ በኪራይ የሚያገኙበት ስትራቴጂ እና ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ ታውቋል፡፡

38. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች ለተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ፡-

- ❖ በአዲሱ ፖሊሲ የጸደቀው  በአዋጅ ተካቶ እንዲጸድቅ ረቂቁ በሚኒስትሮች ምክርቤት ጸድቆ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት  የቀረበ በመሆኑ ለከፍተኛና ለዘርፈ-ብዙ አደጋዎች አስፈላጊ የሆኑ ሎጀስቲክስ/ ሄሊኮፕተር፣ ማሽነሪዎች፣ ሂደቱን ጠብቆ የሚገዙ ሆኖ ከመከላከያ ጋር በትብብር እየተሰራ እንደሚገኝ፡፡
- ❖ ለከፍተኛና ለዘርፈ-ብዙ አደጋዎች የሕይወት አድን ሥራ ለማከናወን ኮሚሽኑ ሁለት አዲስ የሆኑ ጀልባዎች በአምስት ክልሎች ላይ በአፋር፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ጋምቤላ እና ሱማሌ ክልል ከ 7 በላይ ጀልባዎች ያሉ መሆኑን በተጨማሪ በኪራይ አልፎ አልፎ የሚገለገሉበት ሁኔታ መኖሩንና ይህንን ለማሟላት ሰፊ ስራ እየተሰራ እንደሚገኝ፣
- ❖ ከዚህ ቀደም መንግስት ባለው አቅም መሳሪያዎች ለሟሟላት ጥረቶችን ሲያደርግ መቆየቱን፣ በአለም ባንክ ድጋፍ ከ 40 በላይ የተለያዩ ማሽነሪዎች በግዥ ሂደት ላይ እንደሚገኙ ፡-
- ❖ አብዛኛው ከሎጀስቲክ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች አሁን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበው ረቂቅ አዋጅ ሲጸድቅ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነትን ስለሚገልጽ መፍትሔ እንደሚያገኝ ገልጸዋል፡፡

ገልፀዋል፡፡

39. በመሆኑም ህይወት አድን መሳሪያዎችን በኮሚሽኑ ይሁን በክልሎች ካልተገኙ ወይንም ከፍተኛና ዘርፈ ብዙ አደጋዎች ሲከሰቱ በተገቢው ጊዜ የማይገኙ ከሆነ ለተጎጂዎች በአስቸኳይ ለመድረስና አገልግሎት ለመስጠት አዳጋች ያደርገዋል፡፡

**ኮሚሽኑ የቅድሚያ ቅድሚያ ትኩረት የሚገባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ለመለየት የሚያስችል መስፈርት በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፤**

40. ኮሚሽኑ የቅድሚያ ቅድሚያ ትኩረት ምላሽ የሚገባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ለመለየት የሚያስችል መስፈርት ከባለድርሻ አካላት ጋር በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

41. የቅድሚያ ቅድሚያ ትኩረት ምላሽ የሚገባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ለመለየት የሚያስችል መስፈርት ተዘጋጅቷል፡፡ ይሁን እንጂ በኮሚሽኑ የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ወገኖች የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት ተደራሽ መሆኑን ለማረጋገጥ በዕቅድ የያዘ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረባቸው ቃለ መጠይቅ፡- በ2010 ዓ.ም ከሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተፈናቅለው

- ✓ በሐረሪ ክልል (ሐማሬሳ መጠለያ ጣቢያ) 3,310፣
- ✓ በሶማሌ ክልል (ቆሎጂ መጠለያ ጣቢያ) 150,000
- ✓ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሮ ጉቱ ወረዳ በካራሚሌ ከተማ በሚገኙ አራት መጠለያ ጣቢያዎች (ኒጊዴ፣ አልሼኮ፣ ግብርና እና ገንደ ወጋየሁ) 2,679 እንዲሁም
- ✓ በዚሁ ዞን በደደር ወረዳ በሚገኙት ስድስት መጠለያ ጣቢያዎች (ኒው ጎልማሳ፣ ኦልድ ጎልማሳ፣ ኢ.ዲ.ዲ.ሲ.፣ የወጣቶች ማዕከል፣ ውሃ ቢሮ እና ቄይራ) በተሰኙ መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ 6824

በድምሩ ከ162,813 በላይ ወገኖች ተጠልለው የሚገኙ ሲሆን በሶማሌ ክልል መንግስታዊ ያልሆኑ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች (NGOs) ለተፈናቃዮች የሰብአዊ እርዳታ የሚያቀርቡ ሲሆን ከእነዚህ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች እርዳታ በሚቋረጥበት ጊዜ መንግስት እርዳታ የሚያቀረብ ቢሆንም በሌሎቹ መጠለያ ጣቢያዎች ግን ከ2010 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ መጠለያ ጣቢያዎቹ የሚገኙባቸው ክልሎች የሰብአዊ እርዳታ እያቀረቡላቸው የነበረ ሲሆን ከ2015 ዓ.ም. ጀምሮ ግን ክልሎቹ የሚሰጡት እርዳታ የተቋረጠ ስለመሆኑ በኦሮሚያ ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ቡሳ ጎኖፋ ኦሮሚያ የጎሮ ጉቱ ወረዳ ቅርንጫፍ እና የደደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተጠሪዎች እንዲሁም በሐረሪ ክልል የገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት የቅድመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክተር መግለፃቸው፡፡

- ✓ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ተፈናቃይ ወገኖች ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀ ድረስ ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ ያልተደረገ መሆኑ ፣
- ✓ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረረጌ ዞን በካራሚሌ (ኒጊዴ) መጠለያ ጣቢያ እና በደደር (ኢ.ዲ.ዲ.ሲ) በተባሉ መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ ተፈናቃዮች አንድ ትልቅ መጋዘንን በቆርቆሮ በመሸንሸን ተጨናንቀው እንዲቀመጡ የተደረጉ መሆኑ፣



**ፎቶ ቁ.5. በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን በካራሚሌ ከተማ ጎሮጉቱ እና ደደር ወረዳ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያ አንድን መጋዘን በቆርቆሮ በመከፋፈል ከ37 አባወራ በላይ በተፋፈገ ሁኔታ እየኖሩ ስለመሆኑ የሚያሳይ**

የኦዲት ቡድኑ በመስክ ምልከታና በቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

42. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ፡-

- ❖ በሀገር ደረጃ የሰብአዊ ድጋፍ ፍላጎት በየ6 ወሩ በማዘጋጀት እና በየወቅቱ በሚደረግ ዳሰሳ ጥናት በወጣዉ መስፈርት መሰረት ኮሚሽኑ የቅድሚያ ቅድሚያ ትኩረት የሚገባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ለመለየት የሚያስችል መስፈርት በማዘጋጀት በጥናት በተደገፈና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ የተረጂ ቁጥር እንደሚለዩ እና የሚያስፈልገው ሀብትም እንደሚጠየቅ፡፡
- ❖ በ2010 ዓ.ም የነበረው ተፈናቃይ ከሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ብቻ የመጡ ሳይሆን ከሀገረ ሶማሊያ ተፈናቅለው የመጡ መሆኑን እና ድጋፍ እየቀረበላቸው መቆየቱን

❖ በሀማሬሳ ካምፕ ሰፍረው የነበሩ ተፈናቃዮች በርካታ ሲሆኑ በህብረተሰብ ለህብረተሰብ ውይይት አብዛኞዎቹ ወደ ቀያቸው የተመለሱ መሆኑን ቀሪዎቹም ቢሆኑ ከ8 ዓመት በላይ በካምፑ የቆዩ በመሆናቸው አስቸኳይ የሰብአዊ ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሳይሆኑ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው መኖር ያለባቸው ወይንም ወደ ሌላ ቦታ ተወስደው መቋቋም የሚገባቸው እንደሆኑ፣ ካራሚሌና ደደር ከተማ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ የግል ስራቸውን እየሰሩ የሚተዳደሩ መሆኑንና መጠለያዎቹን ለማረፊያነት የሚጠቀሙበት መሆኑን፤ ቀሪዎቹ ባሉበት ዞንና ወረዳ በየዘመድ አዝማድ አካባቢ ተጠግተው የሚኖሩ መሆኑን፤

❖ በሀረሪ ክልል ተፈናቃዮች የሌሉና ከ10 ዓመት በላይ በካምፑ የቆዩ በመሆናቸው አስቸኳይ የሰብአዊ ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሳይሆኑ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው መኖር ያለባቸው ወይንም ወደ ሌላ ቦታ ተወስደው መቋቋም የሚገባቸው እንደሆኑ፣

❖ ምስራቅ ሐረርጌ የሚገኙ ተፈናቃዮች ክልሉ ከአቅሙ በላይ የሆነዉን ጥያቄ ባቀረበባቸዉ የምግብ ማሰራጫ ጣቢያዎች ብቻ ኮሚሽኑ እስከ 2017 ዓ.ም ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ፡፡

❖ በተጨማሪም በመልሶ ማቋቋም ዙሪያ እንደ ሀገር በሁሉም ቦታዎች ሊባል በሚችል መልኩ እየተካሄደ ሲሆን ሙሉ በሙሉ ወደ ነባር ቀያቸው ለመመለስ በተያዘው ዕቅድ መሰረት የተፈናቃይ ሁኔታን ፣ የመንግስት አቅምን ፣ የሀገሪቱ የሰላም ሁኔታን እና የተፈናቃይ ፍላጎትን መሰረት በማድረግ መመለስ የሚችሉትን ወደ ነባር ቦታቸው እንዲመለሱ እየተደረገ መሆኑን እና መመለስ የማይችሉትን ባሉበት ድጋፍ እየተደረገላቸው እንደሚገኝ

ገልፀዋል::

43. የኮሚሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡- የኦዲት ቡድኑ የመስክ እይታ ባደረገበት ጊዜ በሐረሪ ክልል (ሐማሬሳ መጠለያ ጣቢያ) በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው የሚገኙ መሆኑን የተመለከተ በመሆኑ እና ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ ያልተደረገ ስለሆነ በመጠለያ ጣቢያዎቹ የሚገኙት እነዚህ ተፈናቃይ ወገኖች ለረሃብ እና ለተለያዩ ችግሮች እየተጋለጡ ያሉ ሲሆን በአንድ መጋዘን ውስጥ ከሰላሳ ሰባት በላይ አባወራ ለተላላፊና ለወረርሽኝ በሽታ በተጋለጠ ሁኔታ ተጨናንቀው እንዲቀመጡ የተደረጉ በመሆኑ ለከፋ ችግር እንዲጋለጡ እንዲሁም ያለ ስራ ተቀምጠው የሚገኙ እና ቋሚ ገቢ የሌላቸው

በመሆኑም ለአዕምሮ በሽታና የረጅም ጊዜ እርዳታ ጠባቂዎች እንዲሆኑ የተገደዱ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

44. በመሆኑም ኮሚሽኑ እነዚህ የአደጋ ተጎጂና ተፈናቃይ የሆኑ ወገኖችን የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ አቅርቦቶች (መጠለያ ፣ ውሃ ፣ ምግብና ፣ የንፅህናና የጤና አገልግሎቶች ወዘተ…) እንዲሁም በቋሚነት ወደ መደበኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎቻቸው እንዲመለሱ የመልሶ ማቋቋም አገልግሎት የሚያገኙበት ስርዓት በመፍጠር ተግባራዊ ካልተደረገ እነዚህ በርካታ ቁጥር ያላቸው ወገኖች በተለይም ህፃናት ለከፋ ችግርና ህይወታቸውንም እንዲያጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ኮሚሽኑ ለሰብዓዊ እርዳታ የሚውሉ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ጥራታቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑን በተመለከተ

45. ኮሚሽኑ ለሰብዓዊ እርዳታ የሚውል በግዥም ሆነ በዕርዳታ ወደ መጋዘን የሚገቡ/በክምችት ያሉና የሚወጡ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች የጥራት እስፔሲፊኬሽን በማዘጋጀት ጥራታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

46. የኮሚሽኑ የተበላሸ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ከክምችት የሚወገዱበት የውስጥ አሰራር መመሪያ ቁጥር 3/2013 ዓ.ም ገፅ 4፣ ላይ ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር የሚያዙ የተለያዩ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ክምችቶች እንዳይበላሹ በከፍተኛ ጥብቅ ቁጥጥርና ጥንቃቄ መያዝ እንዳለባቸው ሲገልጽ የስርጭት ኮሚቴ ማህበረሰቡን በመወከል የሚሰራጨውን እርዳታ እንዲከታተሉ ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ በስተቀር ሁሉም ከማህበረሰቡ የተውጣጡ መሆን እንደሚገባቸውና የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛም ቁልፍ ሚና እንደሚኖረው በምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ እርዳታ ቁሳቁሶች አስተዳደር ማንዋል (በፌደራልና ክልል መንግስታት በጋራ የተዘጋጀ መመሪያ) ገፅ 1-1 ይገልፃል፡፡

47. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረባቸው ቃለ መጠይቅ፡-

- ❖ በሐረሪ ክልል በሐማሬሳ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃይ ወገኖች መጠኑ እና መቼ እንደቀረበላቸው ያልተገለጸ የተበላሸ ሩዝ የቀረበላቸውና ምርጫ ስለሌላቸው መቀበላቸውን በቃለ መጠይቅ ለማወቅ የተቻለ በመሆኑ ፤
- ❖ እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ለአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በኢሜል ለተላከ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በ2015 ዓ.ም

ከወላይታ ሶዶ መጋዘን ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የተላከው አልሚ ምግብ (መጠኑን ያልገለጹት) የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት ሆኖ መገኘቱ፣

- ❖ በኮሚሽኑ ፕሮግራም ኮሞዲቲ ክትትልና ኢንስፔክሽን በጋምቤላ ክልል የተደረገ የመስክ ጉብኝት ሪፖርት መሰረት የእርዳታ ስርጭት ላይ ሊኖሩ የሚገባቸው የተለያዩ ኮሚቴዎች ስለመኖራቸውና ስለማረጋገጣቸው፣ የቀረበ አቤቱታ መኖር ያለመኖሩን እና የተፈታበትን አግባብ ለማየት የተደረገው ጥረት አሁን ላይ ከማራገፊያ ጣቢያ ወደ ክልሉ የሚመጣ ወረቀት ባለመኖሩ ምንም አይነት መረጃ ያላገኙ መሆኑን

የኦዲት ቡድኑ ባደረገው የመስክ ምልከታ፤ በቃለ መጠይቅ እና ከሰነድ ክለሳ ለማወቅ ተችሏል፡፡

48. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ፡-

- ❖ እህል ሲገባም ሆነ ሲወጣ ከብልሽት ነጻ መሆኑን የጥራት ፍተሻ መደረግ እንዳለበትና ተግባራዊ እያደረጉት የሚገኘዉ የምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ ቁሳቁሶች ጥራት ቁጥጥር የአሰራር መመሪያ 05/2013 ላይ የሚያስቀምጥ መሆኑን፤
- ❖ እህል/ምግብ በክምችት ቆይታ ወቅት ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች ሊበላሽ የሚችልበት ሁኔታ እንደሚኖር ፣ ነገር ግን በክምችት ቆይታ ወቅት እህል/ምግብ ከተበላሸ ለምግብነት የማይዉል መሆኑን ስልጣን ባለው ተቋም እንዲረጋገጥ በማድረግና የተበላሸ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ከክምችት የሚወገድበትን የአሰራር ስርዓት መመሪያ ቁጥር 3/2013 መሰረት በማድረግ ከመጋዘኑ ወደ ተጠቃሚው ህብረተሰብ ወጪ ሳይሆን ህጋዊ ፕሮሲጀሩን ተከትሎ እንዲወገድ እንደሚደረግ፣
- ❖ ነገር ግን በኮሚሽኑ የነሲብ ናሙና አወሳሰድ ዘዴ /Random Sampling Method/ በመጠቀም ፍተሻ ተግባራዊ የሚያደርጉ በመሆኑና ኦፐሬሽኑ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ የተወሰነ ከረጢት እህል ሾልኮ በመውጣት ህብረተሰቡ ጋር ሊደርስ እንደሚችል፣ በመሆኑም ከቅ/ጽ/ቤቶች መጋዘን ወጪ ሆኖ የተላከው ሰብዓዊ እርዳታ የተረከበው የመንግስት አካል ሩዙ መበላሸቱን ለኮሚሽኑ ካሳወቀ ሩዙ ተመላሽ ሆኖ በምትኩ የሚሰጥበት አግባብ መኖሩን፣

- ከላይ ከሐማሬሳ መጠለያ ጣቢያ ጋር ተያይዞ የተጠቀሰው ግኝት ግን አሰራሩን ከማሳየት ውጭ የተበላሸው የሩዝ መጠን፣ የወጣበት ቅ/ጽ/ቤት እና መቼ እንደተሰራጨ መረጃው የሌላቸው በመሆኑ Specific ማድረግ እንዳልቻሉ፡፡
- የምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ ቁሳቁስ ጥራት ቁጥጥር የአሰራር መመሪያ 05/2013 መሰረት እህል ሲገባም ሆነ ሲወጣ ከብልሽት ነጻ መሆን እንዳለበት ገጽ "6" ተ.ቁ 2.1.2. ላይ የሚያስቀምጥ መሆኑን፤
- አልሚ ምግብም ሆነ ሌላ ሰብዓዊ እርዳታ ከኮሚሽኑ ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥቶ በክልሉ በሚገኙ ወረዳዎች ከደረሰ በኋላ ለህብረተሰቡ ሳይሰራጭ መጋዘን የሚቆይበት አግባብ ስላለ አልፎ አልፎ ሳይሰራጭ ሊያጋጥም እንደሚችል ታሳቢ ቢደረግ፤
- እንዲሁም ከላይ በተጠቀሰዉ ምክንያት እንኳን አልሚ ምግቡ ከኮሚሽኑ ቢወጣ፤ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈበት ነው በማለት መረከብ እንደሌለባቸው
- ነገር ግን ከዚህ አልፎ በቸልተኝነት የተፈጠረ የጥራት ቁጥጥር ችግር ካለ ኮሚሽኑ በመመሪያው መሠረት ይህን ባደረገ አካል ላይ የተጠያቂነት አሰራር የሚያሰፍን መሆኑን፣ የወጣው ምግብ በአስቸኳይ ተለይቶ ተመላሽ በማድረግ በአሰራር መሠረት እንዲወገድ እንደሚደረግ ፣ የማከማቻ መጋዘኖች በአግባብ አለመያዝ ካለም ለዚህ ችግር ሊያጋልጥ ስለሚችል ታይቶ የእርምት እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን፣

ገልፀዋል፡፡

49. በመሆኑም ኮሚሽኑ በሁሉም የማሰራጫ ጣቢያዎች የሚሠራጩ የዕርዳታ እህሎች አለመበላሸታቸው ተረጋግጦ ርክክብ ካልተከናወነ እና የስርጭት ኮሚቴ ከማህበረሰቡ እንዲቋቋምና የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ እንዲሳተፍ ካልተደረገ የተበላሸ ወይ የተበከለ የእርዳታ እህል ወደ ተረጂዎች እንዲሰራጭና በዚህም ምክንያት በሚደርስ ችግር ተረጂዎች በተለይ ህጻናትና አረጋውያን ለጤና እክል ሊዳረጉ ይችላል፡፡

## ኮሚሽኑ በቋሚነት ለሰብዓዊ እርዳታ ስራ የሚውል ፈንድ መቋቋሙን በተመለከተ፡፡

50. ኮሚሽኑ ለሰብዓዊ እርዳታ ስራ የሚውል ለአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ፈንድ በቋሚነት የሚቋቋበትን ሁኔታ በማጥናትና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በቅድሚያ ሀብት የሚሰባሰብበት ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

51. ኮሚሽኑ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ሃብት የማፈላለግ ስራ ለመስራት በ10 ዓመቱ (2013-2022) መሪ ዕቅድ ላይ ከ2014-2016 በጀት ዓመት በየዓመቱ አንድ ሀብት ማሰባሰቢያ (የሃብት ግኝት) ፕሮጀክት በመቅረፅ ሃብት ለማሰባሰብ በዕቅድ ይዟል፡፡

52. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረባቸው ቃለ መጠይቅ፡-

- ለአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ፈንድ በቋሚነት የሚቋቋበትን ሁኔታ ኮሚሽኑ ጥናት ያላከናወነ መሆኑ፣
- በኮሚሽኑ 2015 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም መሰረት በዓመቱ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች የሚውል 580.8 ሺህ ሜትሪክ ቶን እህል እና 3.65 ሚልዮን የተለያዩ ቁሳቁሶች በግዢ ለማቅረብ ታቅዶ 180.28 ሜትሪክ ቶን) እና 0.471 (13 በመቶ) ሚልዮን ቁሳቁስ እንደቀደም ተከተላቸው የተገዛ በመሆኑ፡፡
- በ2014 እና በ2015 ዓ.ም በ10 ዓመት ዕቅድ መሰረት ሃብት የማሰባሰብ ስራ ያልታቀደ ሲሆን በ2016 በጀት ዓመት ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ሃብት የማፈላለግ ስራ ለመስራት በኮሚሽኑ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ዕቅዱ ያልተከናወነ መሆኑን ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

53. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ፡-

- ኮሚሽኑ  በሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት ፋይናንስ ጨዋታ ቀያሪ በመሆኑ አሁን አዘጋጅቶ ባቀረበው አዲሱ ረቂቅ አዋጅ አንዱ ትልቅ ትኩረት ከተሰጠው ሥራ ውስጥ አንዱ ዘላቂ የፈንድ ሥርዓት ማቋቋም መሆኑን። በዚህ መሠረት ይህንን ሥርዓት ለመዘርጋት አሁን ላይ በመጨረስ ምዕራፍ ላይ የሚገኝ ሲሆን በቅርብ ወራት ውስጥ አዋጁ ጸድቆ ወደ ሥራ የሚገባበት እንደሚሆንና ይህ ሥራ በተመሳሳይ በክልሎች ደረጃም የራሳቸው የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት በክልል ደረጃ የፈንድ ሥርዓት ለመዘርጋት በአዋጅና በደንብ እያቋቋሙ እንደሚገኑ፣
- ኮሚሽኑ በቋሚነት ለሰብዓዊ እርዳታ ስራ የሚውል ሀብት እና ፈንድ ለማቋቋምና ለማሰባሰብ  ከሚመለከታቸው የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ በመሆን ፕሮጀክት በመቅረጽ በቋሚነት እየሰራ እንደሚገኝ፣ ለአብነት እንደ አገር Humanitarian Response Plan/HRP (የሰብአዊ ምላሽ እቅድ) በአመት 2 ጊዜ በማዘጋጀት ሀብት ለማሰባሰብና ለማስተባበር ጥቅም ላይ እንደሚውል፣ ሀብትም እንደሚገኝበት

❖ የአደጋ ጊዜ የመጠባበቂያ ዕቅድ (Contingency Plan) እና የአለም ባንክ የጎርፍ ፕሮጀክት (World Bank), አውሮፓ ዩኒየን (EU) የተባለ ግብረ ሰናይ ጋር በጋራ በመሆን ብዙ ሥራዎችን እያከናወኑ እንደሚገኙ። ለማሳያነትም በየ6 ወር የሰብአዊ ድጋፍ ፍላጎት ዕቅድ (HRP) በየአመቱ የጎርፍ መጠባበቂያ የሀብት ፍላጎት ሰነዶች መኖሩን፣

ገልፀዋል፡፡

54. በመሆኑም ለሰብአዊ አገልግሎት የሚውል ሀብት በቋሚነት የሚገኝበት ሥርዓት ካልተዘረጋ በልዩ ልዩ ምክንያት ድንገተኛ አደጋ ለሚያጋጥማቸው ዜጎች በአፋጣኝ ተገቢውን የሰብአዊ እርዳታ በራስ አቅም ለማቅረብ እንደ ሃገር የተያዘውን ዕቅድ ለማሳካት አስቸጋሪ ሊያደርገውና ዜጎችም የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ሲከሰት በአፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አቅም እንዳይፈጠርና የሰብዓዊ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው አካላት በአፋጣኝ መድረሰን አዳጋች ያደርገዋል፡፡

**ኮሚሽኑ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ አነስተኛ ክምችት የሚያዝበት ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡፡**

55. ኮሚሽኑ ለድንገተኛ ዕርዳታ እና ለተረጂዎች ለዕለት ድጋፍ የሚውል አስፈላጊ የሆነ የተሟላ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በኮሚሽኑ መጋዘኖች ውስጥ አነስተኛ የክምችት መጠን (Minimum Stock Level) ተወስኖ የሚያዝበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ክልሎችም እንዲሁ አነስተኛ የመጠባበቂያ ክምችል የሚይዙበት ስርዓት እንዲዘረጉ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

56. ይሁን እንጂ፣ በኦዲቱ ወቅት ኮሚሽኑ ባሉት መጋዘኖች ውስጥ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ አነስተኛ ክምችት (Minimum Stock) የሚያዝበት ስርዓት በኮሚሽኑም ሆነ በክልሎች ስለመዘርጋቱ እና ሥርዓቱ ተግባራዊ ስለመድረጉ መረጃ ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

57. በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረባቸው ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የመስክ ጉብኝት ፡-

❖ በኮሚሽኑ የሽንሌ ቅ/ጽ/ቤት (ማዕከላዊ መጋዘን) ለሰብዓዊ እርዳታ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ መጠባበቂያ በመስክ ጉብኝት ወቅት በቅርንጫፍ መጋዘኑ ውስጥ ያልነበረ መሆኑ፣

❖ በሐረሪ ክልል ተረጂዎች (ተፈናቃይ) እርዳታ ጠባቂዎች ቢኖሩም በክልሉ አደጋ ስጋት መጋዘን ውስጥ ከአንድ ዓመት በላይ ምንም አይነት የእርዳታ እህል ወደ መጋዘኑ እንዲገባ ያልተደረገ መሆኑን ክልሉ መግለጹ፣ ሲሆን ኮሚሽኑም ከ2015 በኋላ እርዳታ ወደ ክልሉ ስለመላኩ ወይንም ያልተላከበትን ምክንያት ማስረጃ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣



ፎቶ ቁ.6. በሐረሪ ክልል አደጋ ስጋት አመራር መጋዘን ውስጥ ምንም አይነት ለመጠባበቂያ የሚያገለግል የእርዳታ እህል የሌለ መሆኑን የሚያሳይ

በኦዲቱ ወቅት በተደረገ በመስክ ምልከታና በቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

58. ስለጉዳዩ ለኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ፡-

❖ የካቲት 2016 ዓ.ም የፀደቀዉን የአደጋ ስጋት አመራር ፖሊሲን መነሻ በማድረግ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ መያዝ ያለበትን ዝቅተኛ ክምችት (threshold level) እና የመጋዘን ዲዛይን ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ በመጠናቀቅ ላይ ያለ እና በቅርቡ ፀድቆ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን፡፡

❖ በሽንሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የነበረዉ ክምችት ለክልሎች የተሰራጨ መሆኑን እና በትራንስፈር እና የ2017 ዓ.ም ግዢ ሲፈጸም በፖሊሲዉ መሰረት ክምችት የሚያዝ እንደሚሆን በተጨማሪም የግድ ካልሆነ ደግሞ እንደ የአካባቢው የአየር ንብረት ሁኔታ ሊስተናገድ እንደሚችል

❖ በኮሚሽኑ የክምችት አያያዝ ሥርት መሰረት ክምችት የሚያዘው ለኦፐሬሽን በሚያመችና ወደ ተረጂዎች በቀላሉ ተደራሽ ለመሆን በሚያስችል አኳያ እንጂ የግድ በሁሉም የክምችት መጋዘን ውስጥ ሁሉም ዓይነት ክምችት እንዲኖር አይጠበቅም በማለት ገልፀዋል፡

59. የኮሚሽኑ ኃላፊዎች ይህን ምላሽ ቢሰጡም የኦዲት ቡድኑ የመስክ እይታ ባደረገበት በኮሚሽኑ የሽንሌ ማዕከላዊ መጋዘን እና የሐረሪ ክልል አደጋ ስጋት አመራር መጋዘን ምንም አይነት የእርዳታ እህል የሌለ በመሆኑ ለእነዚህ አካባቢዎች አስቸኳይ እርዳታ ቢያስፈልግ የተያዘ አነስተኛ ክምችት የሌለ በመሆኑ በቶሎ ለተረጂዎች ማድረስ የማይቻል በመሆኑ የተሰጠውን ምልሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

60. በመሆኑም ከሚሽኑ የሰብዓዊ እርዳታን ታሳቢ ያደረገ አነስተኛ የምግብ እና ምግብ ነክ ያልሁኑ ቁሶች ክምችት መጠን (Minimum Stock Level) በራሱ መጋዘኖችም ሆነ በሁሉም ክልሎች የሚያዝበትን አሰራር ዘርግቶ በአፋጣኝ ተግባራዊ የሚደረግበትን ሥርዓት ተግባራዊ አለመደረጉ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ተጎጂ የሚሆኑ ወገኖችን ለመታደግ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

## ኮሚሽኑ በተለያዩ መጋዘኖች የሚገኝ ክምችትን ከብልሽት የሚከላከልበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡፡

61. ኮሚሽኑ በተለያዩ መጋዘኖች የሚገኝ የምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ክምችትን ከብልሽት የሚከላከልበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

62. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረባቸው ቃለ መጠይቅ፡-

- ❖ በኮሚሽኑ ፕሮግራም ኮሞዲቲ ክትትልና ኢንስፔክሽን ክፍል በተደረገ የመስክ ምልከታ ወደ ጋምቤላ ክልል የተላከው የእርዳታ እህል መጋዘን ውስጥ ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ መሬት ላይ ፕላስቲክ ሽት ተነጥፎበት የተቀመጠ መሆኑ፣
- ❖ በኮሚሽኑ ፕሮግራም ኮሞዲቲ ክትትልና ኢንስፔክሽን ክፍል በተደረገ የመስክ ምልከታ ወደ ጋምቤላ ክልል የተላከው የእርዳታ እህል የተቀመጠበት መጋዘን የመያዝ አቅም አነስተኛ መሆኑ
- ❖ በ2015 የኮሚሽኑ ዕቅድ አፈፃፀም ላይ የድሬዳዋ መጋዘን የጣሪያ ጥገና የተከናወነ ስለመሆኑ እና በ2016ትም በዘላቂነት ችግሩን ለመፍታት በዕቅድ ቢያዝም የኦዲት ቡድኑ በጥቅምት ወር 2017 ዓ.ም የመስክ ምልከታ ባደረገበት ጊዜ ችግሩ ያልተቀረፈ መሆኑ፣



ፎቶ ቁ.7. የድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤት (ማዕከላዊ መጋዘን) የእርዳታ እህል ማከማቻ

❖ እንዲሁም የመጋዘን ሰራተኛ መመሪያ ህዳር 2007 ዓ.ም ገፅ 21 ላይ የእርዳታ እህሎችን ከእርጥበት ለመከላከልና በቂ አየር እንዲዘዋወር ድርድሮች ከመሬት ከፍ ባለ ርብራብ (dunnage) ላይ መቀመጥ እንዳለባቸው እና ጥቂት የዕቃ መደርደሪያዎች ብቻ የሚገኙ ከሆነ ለዱቄትና ለቅይጥ/አልሚ ምግቦች ቅድሚያ መሰጠት እንዳለበት ቢገልፅም የኦዲት ቡድኑ የመስክ ምልከታ ባደረገባቸው ሽንሌ፣ ድሬደዋ እና አዳማ መጋዘኖች የእርዳታ እህል አልሚ ምግብ (corn, soya & bean - CSB) ስንዴና መኮረኒ ያለ ፓሌት ፕላስቲክ ሺት ተነጥፎበት ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ የተከማቸ መሆኑ፣



ፎቶ ቁ.8. በአዳማ፣ በድሬደዋ እና በሽንሌ መጋዘኖች የእርዳታ እህል ያለ ፓሌት በፕላስቲክ ሽት የሚቀመጡ መሆኑን የሚያሳይ

በመስክ ምልከታና በሰነድ ክለሳ ለማወቅ ተችሏል፡፡

63. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ፡-

- የካቲት 2016 ዓ.ም የፀደቀውን የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲን መነሻ በማድረግ ተዘጋጅቶ በመጠናቅቅ ላይ በሚገኘዉ የክምችት አስተዳደርና የመጋዘን ዲዛይን ስታንዳርድ ማኑዋል በቅርቡ ፀድቆ ተግባራዊ ሲደረግ፤ እህል እንዴት መደርደር እንዳለበትና በምን መደርደር እንዳለበት፣ ተባይን እንዴት መከላከል እንደሚችል የሚያስረዳ እንደሆነ፤ ሆኖም ግን ለጋምቤላ ክልል የተላከዉ የእርዳታ እህል የተባይ ወረርሽኝ በመከሰቱ የአለም ምግብ ፕሮግራምን በትብብር ህክምና የተደረገለት መሆኑን ፣
- የመጋዘን ሰራተኛ መመሪያ ህዳር 2007 ዓ.ም ገጽ 21 የተጠቀሰዉ የምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ ቁሳቁስ ጥራት ቁጥጥር አሰራር መመሪያ 05/2013 እና የምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ የክምችት ስርጭት መመሪያ 01/2013 የተተካ ነዉ፤ ሆኖም ግን አልሚ ምግብም ሆኑ ሁሉም የምግብ/የእህል አይነት ከፕላስቲክ ሽት ይልቅ ፓሌትን መጠቀም የሚመከር ቢሆንም ከአገልግሎት ጊዜ አጭር መሆኑ (በቀላሉ የሚሰበር) እንዲሁም በቀላሉ የማይገኝ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤት ተደራሽ ማድረግ ያልተቻለ መሆኑን፣
- በክምችት መጋዘን ውስጥ የሚከማቹ ምግቦችን በፕላስቲክ ሺት ላይ መደርደር በአሰራሩ የሚፈቀድ መሆኑን ይህን ያክል ችግር ያመጣል ተብሎ እንደማይገመት ፣ ነገር ግን አሁን የተደረደረበት ሁኔታ ችግር የሚያመጣ ሆኖ ከተገኘ ኮሚሽኑ በፓሌቶች ላይ እህሉ እንዲደረደር የሚደረግ መሆኑንና የሚመለከተው የስራ ክፍልም ይህን ወስዶ የእርምት እርምጃ የሚወስድ ይሆናል

በማለት ገልፀዋል፡፡

64. የኮሚሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡-

- የመጋዘን ሰራተኛ መመሪያ ህዳር 2007 ዓ.ም ገጽ 21 የተጠቀሰው የምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ ቁሳቁስ ጥራት ቁጥጥር አሰራር መመሪያ 05/2013 እና የምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ የክምችት ስርጭት መመሪያ 01/2013 የተተካ መሆኑ በሃላፊዎች ቢገለፅም በነባሩም ሆነ በአዲሱ መመሪያ ማለትም የክልሎች የመጋዘን ዲዛይንና የክምችት አስተዳደር ስርዓት ስታንዳርድ ማኑዋል ታህሳስ 2017 ዓ.ም ክፍል አራት ገፅ 24 ላይ ምግብና ቁሳቁስ ወደ መጋዘን በሚገባበት

ወቅት የሚደረግ ጥንቃቄን ሲገልፅ በቂ የሆነ ፓሌት (dunnage) መኖሩን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ የሚገልጽ በመሆኑ የተሰጠውን ምልሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

65. በመሆኑም

❖ የድሬዳዋ መጋዘን የጣሪያ ጥገና በዘላቂነት ችግሩ በአፋጣኝ ካልተፈታ፣ እንዲሁም ኮሚሽኑ የሰብዓዊ እርዳታ እህልን ወደ ክልሎች ሲልክ ክልሎች በቂ መጋዘን ማዘጋጀታቸውን ካላረጋገጠ እና የመያዝ አቅምን ከግምት ያስገባ ካልሆነ እንዲሁም ወደ መጋዘኖች የሚገቡ እህሎች የእህል መደርደሪያ ፓሌት ላይ ካልተቀመጡ የእርዳታ እህሉ ለብልሽት ሊዳረግና ለተፈለገው ዓላማ እንዳይውል ያደርጋል፡፡

## ኮሚሽኑ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡፡

66. ኮሚሽኑ ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር የሚያገለግሉ የአደጋ ጊዜና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ዘመናዊ የመገናኛ መሳሪያዎች እና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት በመዘርጋት አፋጣኝ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

67. የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ (2013-2022) የአደጋ መጠቆሚያ መሳሪያዎችን በመጠቀም የአደጋ መንስዔዎችን ድግግሞሽና መጠን ለመከታተልና ለመቆጣጠር ታቅዷል፡፡

68. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረባቸው ቃለ መጠይቅ፡-

❖ በኮሚሽኑ የ10 ዓመት (2013-2022) መሪ ዕቅድ ወደ አመታዊ ዕቅድ ተመንዝሮ ስለመታቀዱ እንዲሁም በእቅድ ከተያዘ ደግሞ ስለመተግበሩ ማስረጃው ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልቀረበ መሆኑ

❖ በኮሚሽኑ ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር የሚያገለግሉ የአደጋ ጊዜና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ካሜራዎች፣ የመገናኛ ሬድዮና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ቴክኖሎጂ ያልተሟሉና በክልል አደጋ ስጋት ቢሮዎችም በዚህ ደረጃ ያልተደራጁ መሆኑ

በመስክ ምልከታና በሰነድ ክለሳ ለማወቅ ተችሏል፡፡

69. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ፡-

- ❖ ኮሚሽኑ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ ዙሪያ ከፌዴራል ጀምሮ እስከታችኛው መዋቅር ለመናበብ፤ መረጃ ለመለዋወጥ፤ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሰርዓት በበለጠ ዘመናዊ ለማድረግ ስራዎች ሲሰሩ መቆየታቸውን፡፡
- ❖ ፍኖተ ካርታ (A roadmap for multi-hazard, impact-based early warning 2023-2030_Building disaster resilient communities in Ethiopia) አዘጋጅቶ ወደ ተግባር መግባቱን፡
- ❖ የወረዳ ኔት ስርዓት እስካሁን 148 ወረዳዎች ላይ የተዘረጋ ሲሆን የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃ ለመሰብሰብ እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ፣ የሚገኘው ሀብትና በመንግስት አቅም ለወደፊት እየተስፋፉ እንደሚሄድ ጅምሩ ያለ መሆኑን ፡፡
- ❖ የሬድዮና የተግባር ቴክኖሎጂዎችን ለማስተከል ከአለም ባንክ በተገኘ ድጋፍ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች መጠናቀቃቸውን፤
- ❖ በፌደራል እና በ4 ክልሎች (የክልሎቹ ስም አልተጠቀሰም) የቅድመ ማስጠንቀቂያ የክስተት ሁኔታ መምሪያ ቴክኖሎጂዎችና የኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች መገጠማቸውን ፡፡
- ❖ በተጨማሪም በማዕከል ሁኔታዎችን መከታተያ (Situation room) ግንባታ ለማካሄድ ቅድመ ዝግጅት ስራዎች መጠናቀቃቸውን፣ ይህም ሲጠናቀቅ የቅፅበታዊ ጊዜ መረጃን ለማጠናከር በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ እንደሚደረግ
- ❖ በተለያየ ሥፍራዎች የሚፈጠሩ አደጋዎችን የሚያሳይ የሚጠቁም ሰሌዳ (Shock response dashboard) ተጠናቆ ሥራ የጀመረ መሆኑን፣
- ❖ ኮሚሽናቸውም የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት በመዘርጋት ማህበረሰብን ስለ አደጋ ቅድመ ግንዛቤ እንዲኖረው ከሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች ጋር በመሆን ሰፊ ሥራዎችን እየሰራ እንደሚገኝ። በተለይም ይህ ሥራ የግንዛቤ ፈጠራን በተደጋጋሚ ለባለሙያዎችና ለማህበረሰቡ መፍጠርን የሚጠይቅ በመሆኑ ይህንኑ ሥራ ኮሚሽኑ በትኩረት እየሰራ እንደሆነ። በተጨማሪም ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ ያለውን መዋቅር በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራው እየተሰራ እንደሚገኝ፣ እንዲሁም ለክልሎች የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት መረጃዎችን በስልጠና፣ በዌብሳይት፣ በማህበራዊ ሚዲያና በቴሌቪዥኖች እንዲተላለፍ መደረጉን ይህም በቀጣይነት የሚቀጥል ይሆናል

በማለት ገልፀዋል፡፡

70. በመሆኑም በሁሉም የሃገሪቱ ክልሎች እነዚህ ለአደጋ ጊዜ ቅድመ ማስጠንቀቂያ የሚረዱ መሳሪያዎች ተተክለው ወደ ስራ በማስገባት አገልግሎቱን ማቅረብ ካልተቻለ የተፈጥሮ አደጋዎችን ቀድሞ በመተንበይ ለመዘጋጀት፣ የመከላከል ስራውን ለመስራትና በተቀናጀ ሁኔታ ዕርዳታ የማድረስ ሁኔታን ከባድ ያደርገዋል፡፡

## በኮሚሽኑ የሚከናወኑ የመጋዘን ግንባታዎች በተመለከተ፡፡

71. በኮሚሽኑ የሚከናወኑ ግንባታዎች በተያዘላቸው በጀትና ጊዜ ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት ሊጀምሩ ይገባል፡፡ ይህን ለማከናወንም ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

72. የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ (2013-2022) ገፅ 78 ላይ ኮሚሽኑ የዕቅድ አፈፃፀሙን ለመለካትና ሊደረስበት የታሰበውን ግብ መከናወኑን፣ የፕሮጀክት አፈፃፀሙን፣ የበጀት ግኝትንና አጠቃቀሙን ለመከታተል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት እንደሚዘረጋ ቢገልፅም

73. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረባቸው ቃለ መጠይቅ፡- የሦስት የመጋዘን ግንባታዎች እየተከናወኑ የነበረና ከ2010 እስከ 2016 በጀት አመታት (ለፍኖተ ሰላም፣ ለቀብሪ ደሃርና ለሆሳዕና መጋዘኖች ግንባታ የአፈር ምርመራን ጨምሮ) በድምሩ ብር 3,809,378,910 በጀት የታወጀላቸው ቢሆንም (የተመደበ በጀት በአባሪ 8 እና የበጀት አፈጻጸም በአባሪ 9 ይመልከቱ)

ከላይ ለተጠቀሱት ሶስት መጋዘኖች ግንባታ ለማከናወን በመጀመሪያው የውል ስምምነት እያንዳንዱን ፕሮጀክት አጠናቆ ለማስረከብ ውል የተገባባቸው የገንዘብ መጠን እና

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ስም | ውል የተገባበት የገንዘብ መጠን (በብር) | የተጀመረበት ቀንና ዓ.ም | የሚጠናቀቅበት ቀንና ዓ.ም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ፍኖተሰላም የእህል መጋዘን ምድረ ግቢና ሌሎች ተዛማች ህንፃዎች ግንባታ | 1,051,858,096.02 | ሰኔ 27, 2010 (July 04,2018) | ሚያዝያ 2013 ዓ.ም (3 ዓመት) |
| 2 | ቀብሪድሃር የእህል መጋዘን ምድረ ግቢና ሌሎች ተዛማች ህንፃዎች ግንባታ | 342,303,773.02 | ሰኔ 27, 2010 (July 04,2018) | ሚያዝያ 2013 ዓ.ም (3 ዓመት) |
| 3 | ሆሳዕና የእህል መጋዘን ምድረ ግቢና ሌሎች ተዛማች ህንፃዎች ግንባታ | 998,496,884.05 | ጥር 1, 2012 (Jan10,2020) | ጥር 2015 ዓ.ም (3 ዓመት) |

ግንባታዎቹ የሚጠናቀቁበት ጊዜ በሰንጠረዥ ተመላክቷል፡፡

ከላይ በሰንጠረዥ እንደተመለከተው እነዚህ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው በጀትና ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ የሚገባቸው ቢሆንም ይህ ባለመሆኑ ምክንያት አዲስ የውል ስምምነት የተፈፀመላቸው ሲሆን ከታች በሰንጠረዥ ተመላክቷል፡፡

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ስም | ውል የተገባበት የገንዘብ መጠን (በብር) | የተጀመረበት ቀንና ዓ.ም | የሚጠናቀቅበት ቀንና ዓ.ም | ግንባታው ህዳር 30/2017 ያለበት ደረጃ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ፍኖተሰላም የእህል መጋዘን ምድረ ግቢና ሌሎች ተዛማች ህንፃዎች ግንባታ | 6,555,000,000.00 | ሚያዝያ 20, 2015 ዓ.ም (Apr 28,2023) | ሚያዝያ 20,2017 ዓ.ም (2 ዓመት) | 49.24% | የመጀመሪያው ውል ካበቃ ከ2 ዓመት በኃላ የተገባ ውል |
| 2 | ቀብሪድሃር የእህል መጋዘን ምድረ ግቢና ሌሎች ተዛማች ህንፃዎች ግንባታ | 626,718,375.66 | ግንቦት 23, 2016 ዓ.ም (May 31,2024) | ግንቦት 23,2017 ዓ.ም (1 ዓመት) | 71.5% | የመጀመሪያው ውል ካበቃ ከ3 ዓመት በኃላ የተገባ ውል |
| 3 | ሆሳዕና የእህል መጋዘን ምድረ ግቢና ሌሎች ተዛማች ህንፃዎች ግንባታ | 4,305,357,765.23 | ግንቦት 28,2016 ዓ.ም (June 5,2024) | ግንቦት 28,2018 ዓ.ም (2 ዓመት) | 34.47% | የመጀመሪያው ውል ካበቃ ከ1 ዓመት በኃላ የተገባ ውል |

በመሆኑም ሶስቱ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ባለመጠናቀቃቸው ምክንያት አዲስ ውል የተገባ በመሆኑና ይህም አዲስ ውል ፕሮጀክቶቹ ከተያዘላቸው 3 ዓመት መጠናቀቅ በኋላ በአማካኝ ከሁለት ዓመት በላይ ዘግይተው ከተቋራጮች ጋር ውል የተገባላቸው በመሆኑ፡-

- ❖ የፍኖተሰላም የእህል መጋዘን ምድረ ግቢና ሌሎች ተዛማች ህንፃዎች ግንባታ፡- በመጀመሪያው ውል ከተያዘለት ብር 1,051,858,096.02 ወደ 6,555,000,000.00 በማደግ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ያመጣ መሆኑ
- ❖ የቀብሪድሃር የእህል መጋዘን ምድረ ግቢና ሌሎች ተዛማች ህንፃዎች ግንባታ፡- በመጀመሪያው ውል ከተያዘለት ብር 342,303,773.02 ወደ 626,718,375.66 በማደግ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ያመጣ መሆኑ
- ❖ የሆሳዕና የእህል መጋዘን ምድረ ግቢና ሌሎች ተዛማች ህንፃዎች ግንባታ፡- በመጀመሪያው ውል ከተያዘለት ብር 998,496,884.05 ወደ 4,305,357,765.23 በማደግ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ያመጣ መሆኑ
- ❖ የፍኖተሰላም የእህል መጋዘን ምድረ ግቢና ሌሎች ተዛማች ህንፃዎች ግንባታ በመጀመሪያ ውል ከያዘው ተቋራጭ ዞንግያንግ ኮንስትራክሽን ግሩፕ (ZHONGYANG CONSTRACTION GROUP CO.LTD) ከተባለ ድርጅት ጋር የነበረው ውል የተቋረጠ ሲሆን ኦቪድ ኮንስትራክሽን ኃላ.የተ.የግ.ማህበር (Ovid Construction PLC) ከተባለው ድርጅት ጋር ያለ ውድድር አዲስ ውል የተገባ መሆኑ

- ❖ ፕሮጀክቶቹ አሁን ከደረሱበት አፈፃፀም አንፃር በቀሪዎቹ የውል ጊዜያት ይጠናቀቃሉ ተብሎ የማይታሰብ መሆኑ
- ❖ የፍኖተ ሰላም የመጋዘን ግንባታ የተጀመረበት ቀን እ.አ.አ. july 04,2018 ሲሆን የሚጠናቀቅበት ቀን june 01,2025 ቢሆንም እስከ ህዳር 30/2017 ዓ.ም ድረስ አፈፃፀሙ 49.24% መሆኑ፣ ከኮሚሽኑ የፋሲሊቲ ግንባታ ክብካቤና አስተዳደር መሪ ክፍል መረጃ መቅረቡ፣
- ❖ የቀብሪደሃር የመጋዘን ግንባታ የተጀመረበት ቀን እ.አ.አ. july 04,2018 ሲሆን የሚጠናቀቅበት ቀን May 31,2025 ቢሆንም እስከ ህዳር 30/2017 ዓ.ም ድረስ አፈፃፀሙ 71.5% ሲሆን በ2016 በጀት ዓመት የግንባታ ስራው ያልተከናወነ ስለመሆኑ ከኮሚሽኑ የ2016 ዕቅድ አፈፃፀም የተገለፀ መሆኑ፣
- ❖ የሆሳዕና የመጋዘን ግንባታ የተጀመረበት ቀን እ.አ.አ. February 10,2020 ሲሆን የሚጠናቀቅበት ቀን April 29,2026 ቢሆንም እስከ ህዳር 30/2017 ዓ.ም ድረስ አፈፃፀሙ 34.47% መሆኑ
- ❖ የኮሚሽኑ የፕሮጀክት አፈፃፀሙን፣ የበጀት ግኝትንና አጠቃቀሙን ለመከታተል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ስለመዘርጋቱ መረጃ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል

74. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ፡-

- ❖ የፍኖተሰላም መጋዘን ግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም ዝቅተኛ የሆነው
  - ✓ ከመጀመሪያ ጀምሮ የወሰን ማስከበር ችግር የገጠመው መሆኑን
  - ✓ ከፍተኛ ኃይል (ቮልቴጅ) ተሸካሚ የኤሌክትሪክ መስመር አቋርጦት የሚያልፍ በመሆኑ የኤሌክትሪክ መስመሩን ለማንሳት በፕሮጅክቱ ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ከፍተኛ መጓተት መፍጠሩን፣
  - ✓ ኮቪድ 19 በፕሮጀክቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ በመፍጠሩ በታቀደለት የስራ መርሃ ግብር መሄድ አለመቻሉን፣
  - ✓ የሰሚኑ ጦርነትና የዋጋ ንረት (Inflation) በፕሮጀክቱ ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ተፅዕኖ የፈጠረ መሆኑን፣
  - ✓ የሥራ ተቋራጩ ሥራውን በተቀመጠለት የጊዜ ሠሌዳ መሰረት ለመስራት አዳጋች ስለነበረም ውሉ በሚፈቅደው መሰረት ውሉን በማቋረጥ ፕሮጀክቱ ለሌላ ሥራ ተቋራጭ እንዲሰጥ መደረጉን፣ እና

- ✓ በአሁኑ ወቅትም በአካባቢው ባለው የሰላም እጦት ምክንያት ችግሩ ብዙም ያልተቀረፈ መሆኑን፣
- ❖ የቀብሪደሃር መጋዘን ግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያቶች
  - ✓ ፕሮጀክቱ መጀመሪያ ሊገነባበት ከታሰበው ቦታ በመቀየሩ ተጨማሪ ጥናት በማስፈለጉ፣
  - ✓ ለሁለተኛ ጊዜ የዲዛይንና የአፈር ምርመራ የተሰራ መሆኑን፣
  - ✓ የዋጋ ንረት (Inflation)፣ ኮቪድ 19፣ የችክንጉንያ ወረርሽን እና የስሚንቶ እጥረት ማጋጠሙን፣
  - ✓ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ሙሉ በጀት ባለመለቀቁ በፕሮጀክቱ ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማስከተሉን፣
- ❖ የሆሳዕና መጋዘን ግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያቶች
  - ✓ ፕሮጀክቱ የወሰን ማስከበር ችግር (የሰባት መጋዘን ቦታ እስከሁን ያልተሰጣቸው በመሆኑ)፣
  - ✓ የዋጋ ንረት (Inflation)፣ ኮቪድ 19 እና የስሚንቶ እጥረት በማጋጠሙ በፕሮጀክቱ ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ከፍተኛ መጓተት መፍጠሩን፣
- ❖ ፕሮጀክቶቹ የኢትዮጵያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የሕንፃና ከተማ ዘርፍ በአማካሪ ድርጅትነት የሚቆጣጠረው ሲሆን የፕሮጀክት አፈፃፀሙን፣ የበጀት ግኝትንና አጠቃቀሙን ለመከታተል የሚያስችል የመንግስት ግዥ መመሪያ፣ የኮንስትራክሽን ቁጥጥር ባለስልጣን ማኑዋሎችና ስታንዳርድስ፣ ፎርማቶችና ቼክሊስቶች የአሰራር ስርዓት የሚከተል መሆኑን እና ሁሉም ፕሮጀክቶች የነበሩባቸው ችግራቸው ተፈቶ በአሁኑ ጊዜ ወደ ስራ መግባታቸውን

ገልፀዋል፡፡

75. የኮሚሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡-

- ❖ ኮሚሽኑ የፍኖተሰላም የእህል ማከማቻ መጋዘን፣ የቢሮ እና የመሳሰሉት ግንባታዎች ፕሮጀክቱ ሲጀመር ግንባታው አጠቃላይ ከሚያርፍበት ቦታ ውስጥ 26 በመቶ ብቻ ነፃ የነበረ እና ሙሉ ለሙሉ የወሰን ማስከበር ስራ ሳይከናወን ወደ ውልና ግንባታ የተገባ በመሆኑ፤
- ❖ ኮሚሽኑ የቀብሪደሃር የእህል ማከማቻ መጋዘን፣ የቢሮ እና የመሳሰሉት ግንባታዎች ይዞታ ሙሉ ለሙሉ ባለመከበሩ እንዲሁም "Access to the Site" ባለመከበሩ እና ግንባታው ሳይሰራ ከሁለት ዓመት በላይ በመቆየቱ፤

❖ እንዲሁም የሆሳዕና የእህል ማከማቻ መጋዘን፣ የቢሮ እና የመሳሰሉት ግንባታዎች ግንባታው ከሚከናወንበት ጠቅላላ የቦታ ይዞታ 21 ሄክታር ውስጥ 2/3ኛው ብቻ ነፃ ተደርጎ ወደ ስራ የተገባ በመሆኑ፣

❖ በአጠቃላይ ሶስቱም ግንባታዎች ከመነሻቸው ሲጀመሩ የወሰን ማስከበር ችግር ያለባቸው መሆኑ እየታወቀ እና ይህም ችግር ሳይፈታ ወደ ውልና ግንባታ የተገባ በመሆኑና ግንባታዎቹ በተያዘላቸው ጊዜ የማይጠናቀቁ በመሆኑ፤

❖ በአጠቃላይ ሶስቱ ፕሮጀክቶች መጀመሪያ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ቢጠናቀቁ ብር 2,392,658,753.09 (ሁለት ቢሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃምሳ ስምንት ሺ ሰባት መቶ ሃምሳ ሶስት) ወጪ ብቻ ይጠይቁ የነበረ ቢሆንም በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ባለመጠናቀቃቸው መንግስትን ተጨማሪ 9,094,417,387.08 (ዘጠኝ ቢሊዮን ዘጠና አራት ሚሊዮን አራት መቶ አስራ ሰባት ሺ ሶስት መቶ ሰማንያ ሰባት) ብር ወጪ እንዲያወጣ ያደረገ በመሆኑ፣

❖ በተቋሙ የፕሮጀክት አፈፃፀም፣ የበጀት ግኝትንና አጠቃቀሙን፣ ለመከታተል የሚያስችል ለአፈፃፀም ክትትል የሚረዳ አስገዳጅ (statutory) የአሰራ ስርዓት ለመዘርጋት በ10 ዓመት ዕቅዱ አቅዶ ያላከናወነ በመሆኑ

የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

76. በመሆኑም ግንባታዎች ከመጀመራቸው በፊት ሙሉ ለሙሉ የፕሮጀክቶቹ ይዞታ ካልተከበረና እና በጊዜውም ግንባታዎች የማይጀመሩ ከሆነ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ እንዳይጠናቀቁ ሊያደርግና እነዚህ ሶስት ፕሮጀክቶችም በአዲሱ ውል መሰረት በተያዘላቸው ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ አስፈላጊው የፕሮጀክት ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገባቸው ለሌላ የህዝብ አገልግሎት የሚውል ሀብት እንዲይዝ፣ እንደ መጀመሪያው ውል መንግስትንም ፕሮጀክቱ በመዘግየቱ ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርግ እንዲሁም ፕሮጀክቶቹ ተጠናቀው ለህብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት እንዳይሰጡ ያደርጋል፡፡

**ኮሚሽኑ የእርዳታ እህልና ቁሳቁስን ያለ አግባብ ላልተገባ ዓላማ እንዳይውል ለመከታተል የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡፡**

77. ኮሚሽኑ የእርዳታ እህልና ቁሳቁስን ያለ አግባብ ላልተገባ ዓላማ እንዳይውል ለመከታተል የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

78. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረባቸው ቃለ መጠይቅ፡-

- ❖ የፕሮግራምና ኮሞዲቲ ክትትልና ቁጥጥር የአሰራር መመሪያ ቁ.1 ተዘጋጅቷል፡፡ ነገር ግን የተዘጋጀው መመሪያ ግን ወደ ተግባር ስለመግባቱ ማስረጃ ያልቀረበ እና በአንዳንድ አካባቢዎች የተላኩት ድጋፎች ለታለመላቸው ተረጂዎች ሳይደርሱ በገበያዎች፣ በሱቆች እና በወፍጮ ቤቶች የታዩ መሆኑን በኮሚሽኑ ከ2015 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ❖ ኮሚሽኑ ለሰብአዊ ዕርዳታ የሚሆን ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን በተለያየ ቦታ ካሉት መጋዘኖቹ ለክልሎች ከላከ በኋላ በትክክል ስለመድረሱና ለተረጂዎች ስለመከፋፈሉ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ያልዘረጋ እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ የመስክ ምልከታ ባደረገባቸው በሐረር፣ በካራሚሌ እና ደደር ወረዳዎች ለእለት እርዳታ የሚላከው ድጋፍ ለተጠቃሚው ስለመድረሱ ተገቢ የክትትልና የድጋፍ ስራ አለመከናወኑን፣
- ❖ የሰብዓዊ ድጋፍ እርዳታን ለታለመለት ዓላማ ብቻ ማዋል እንዲቻል
  - ❖ ብሔራዊ የትኩረት የሚደረግባቸው መመሪያ (National Targeting Guideline) ክለሳ ላይ መሆኑን
  - ❖ የቤተሰብ ኢኮኖሚ አቅም መለያ (Household Economic Approach) (HEA) ቤዝ ላይን ክለሳ ላይ መሆኑን
  - ❖ ተጋላጭነትን መሰረት ያደረገ ልየታ (Vulnerability Based Targeting) (VBT) ትግበራ መመሪያ ተዘጋጅቶ በሙከራ ደረጃ ያለ መሆኑን
  - ❖ የተጠቃሚዎች ምዝገባ ስርዓትን ዲጂታላይዝድ የማድረግና ከብሔራዊ የመታወቂያ ፕሮግራም ስርዓት ጋር የማያያዝ ስራ በፓይለት ደረጃ ላይ ያለ መሆኑ

ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር ምክር ቤት የቀረበ የ2016 በጀት ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርት ሰነድ ላይ ሥርዓቱን ለማስጀመር በቅድሚያ የተሰሩ ተግባራት ተብለው የተገለጸ መሆኑ፣

በመስክ ምልከታና ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

79. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ፡-

- ❖ የፕሮግራም ኮሞዲት ክትትልና ቁጥጥር መመሪያ መስከረም 8 ቀን 2017 ዓ.ም. በረቂቅ ደረጃ ጸድቆ ወደ ስራ መግባቱን የፀደቀውን ሰነድ ያቀረቡ ሲሆን፣ የክልሎች የእርዳታ ስርጭት ክትትልና ድጋፍ ማድረግን በተመለከተ የክልሎች የአጠቃቀም ሪፖርት ከቀረበ በኃላ ክትትል የሚደረግ በመሆኑ ለተረጂዎች እርዳታው በትክክል ስለመድረሱ ተረጂውን በማናገር ክፍተቶች የሚለዩበት አሰራር መዘርጋቱን ገልፀዋል፡፡
- ❖ በተጨማሪም ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ላይ የእርዳታ እህልና ቁሳቁስን ያለ አግባብ ላልተገባ ዓላማ እንዳይውል ብልሹ አሰራሮችንና የሌብነት ተግባርን ለማረምና ቁጥጥር ለማድረግ አንድ የስራ ክፍል ይህን ብቻ የሚሰራ የሎጀስቲክስ ኢንስፔክሽን መሪ ሥራ አስፈጻሚ በማቋቋም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ ሥራ መግባት መቻሉን። ይህ የሥራ ክፍል አሁን ላይ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋትና በሰው ሀይል በማደራጀት እስከ ምግብ ማሰራጫ ጣቢያ ድረስ በመውረድ የቁጥጥር ሥራዎች እየሰራ በሚያገኛቸው ግኝቶች ከአመራሮች ጋር የጋራ በማድረግ ግብረ መልስ የመስጠት ሥራ እየሰራ ይገኛል በማለት ገልጸዋል፡፡

80. በመሆኑም ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተጀመሩ ስራዎች በሁሉም ክልሎች በተሟላ ሁኔታ ወደ ስራ እንዲገቡ ካልተደረገ በድንገተኛ አደጋዎች ምላሽ አሰጣጥና በመሰረታዊ የዕለት ዕርዳታ አቅርቦቶች እጦት ወይም እጥረት ምክንያት የተረጂ ወገኖች ህይወት አደጋ ላይ ሊወድቅና ብሎም መንግስትን ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

## ኮሚሽኑ የየአመት ዕቅድ አፈፃፀሙን ከባለድርሻ ፣ ከአጋር አካላት ፣ ከክልሎች እና ከተረጂ (ተፈናቃይ) ወገኖች ጋር በጋራ መገምገሙን በተመለከተ፡፡

81. ኮሚሽኑ የየአመት ዕቅድ አፈፃፀሙን ከባለድርሻ አካላት፣ ከአጋር አካላት እና ከክልሎች ጋር በጋራ ሊገመግም ይገባል፡፡

82. ኮሚሽኑ የየዓመት ዕቅድ አፈፃፀም በአመራሩ፣ በህዝብ ክንፍ፣ በአጋር አካላት እና በክልሎች ይገመግማል፡፡

83. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረባቸው ቃለ መጠይቅ፡- በኮሚሽኑ የ2015 በጀት ዓመት የሁለተኛው ግማሽ ዓመት የተከለሰ ዕቅድ ገፅ 10 ላይ ከተረጂዎች (ተፈናቃይ) ጋር ምክክርና ውይይት በማካሄድ ችግሮቻቸውን ለመፍታት በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ኮሚሽኑ በዕቅዱ መሰረት ተረጂዎች ያለባቸውን ችግር ለመፍታት እንዲቻል ከተረጂዎች (ተፈናቃይ ወገኖች) ጋር ምክክርና ውይይት የማያደርግ መሆኑ

በኦዲቱ የመስክ እይታና ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

84. ስለጉዳዩ ለኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ፡-

- ❖ በኮሚሽኑ እቅድ እንደተቀመጠው ኮሚሽኑ ከተፈናቃዮች ጋር ውይይት የሚያደርግ ሲሆን ውይይቱ የተረጂዎችን ችግር ለመፍታት በተከታታይ ተፈናቃዮች ባሉባቸው አካባቢዎች የቡድን አባላት በመላክ ውይይት በማድረግ የመፍትሔ አቅጣጫ እንደሚቀመጥ፡፡
- ❖ በጉዳዩም ላይ ከክልል አመራሮች ጋር የጋራ መደረኮችና ጉባዔ በማዘጋጀት ተገምግሞ የመፍትሄ አቅጣጫም የሚቀመጥ መሆኑን፣
- ❖ በተጨማሪም ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ ምላሽ ሲሰጡ ኮሚሽኑ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በአጠቃላይ የኮሚሽኑ ሥራዎች ላይ በመገናኘት ውይይቶችን እንደሚያደርግ ፣ዕቅዱን በመከለስ አፈጻጸሙን በተለያዩ መንገዶች በመገምገም የጋራ እንደሚያደርጉ፣

ገልፀዋል፡፡

85. የኮሚሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ይህን ይበሉ እንጂ፡-

- ❖ ኮሚሽኑ የ2015 በጀት ዓመት የ6 ወራት ዕቅድ አፈፃፀም የምክክር መድረክ ከየካቲት 01-06-2016 ዓ.ም የተዘጋጀ መድረክ፣ በትግራይ ክልል በግጭት ምክንያት ተፈናቅለው ወደ ቀያቸው የተመለሱ ወገኖች ያሉበትን ሁኔታ በመመልከት የተዘጋጀ ሪፖርት፣ በሶማሌና አፋር ክልሎች የተካሄደ የምክክር መድረክ መረጃዎች እንዲሁም ከጤና ሚኒስቴር፣ ከግብርና ሚኒስቴር፣ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ የሰላም ሚኒስቴር፣ የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር፣

የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴር የከተማና መሰረተ-ልማት ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር የሃገር መከላከያ ሚኒስቴር እና ከመሳሰሉት ከባለድርሻ አካላት ጋር አመታዊ ዕቅዱን የገመገመ ቢሆንም በግምገማዎቹ ውጤት መሰረት እርምጃ ተወስዶ ችግሮቹ ስለመቀረፋቸው ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

86. በመሆኑም ኮሚሽኑ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር እንዲሁም ተፈናቃይ ወገኖችን በአካል በመገኘት እና ውይይቶችን በማዘጋጀት ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ ጥረት የማይደረግ ከሆነ ችግሩን መቅረፍ አዳጋች የሚያደርግና ቀድሞ ከነበሩበት ቀያቸው ተገፍተው የተፈናቀሉ ወገኖች ተገቢውን ድጋፍ እንዳያገኙ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ኮሚሽኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን ለማጓጓዝ የትራንስፖርት አገልግሎት ግዥ አፈጻጸምን በተመለከተ፣

87. ኮሚሽኑ ምግብ ነክ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን ወደ ቅርንጫፍ (ማዕከላዊ) መጋዘኖች ለማጓጓዝ ለትራንስፖርት አቅራቢዎች ጨረታ በማውጣት አገልግሎቱን ሊገዛ ይገባል፡፡ ከውድድሩ አሸናፊዎቹ ጋር ውል በመፈራረም በገቡት ውል መሰረት አገልግሎቱን ማቅረባቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

88. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- የግል የትራንስፖርት አቅራቢዎች በጨረታ የሚመረጡ እና ውል የሚገባ መሆኑ፣
- ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ለአፋርና ሶማሌ ክልሎች የእርዳታ እህልና ቁሳቁስ ካጓጓዘው የዕለት ደራሽ የዕርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት ከሚባል የመንግሰት ተቋም ጋር የተገባ የውል ስምምነት ያልቀረበ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

89. ስለጉዳዩ ለኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ፡-

- ❖ ኮሚሽኑ ምግብ ነክ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን ወደ ቅርንጫፍ (ማዕከላዊ) መጋዘኖች ለማጓጓዝ የጨረታ ሂደትን የሚከተል እንደሆነና ማንኛዉም ትራንስፖርት አቅራቢዎች በጨረታ ተለይተው ግልጽነት ባለው መንገድ ግዥ

ተፈጽሞ የውል ስምምነት ሳይፈርሙ ስምሪት የማይሰጣቸዉ መሆኑን እና ማንኛዉም ክፍያ ጨረታ ባሸነፈዉ ዉል መሰረት መሆኑን፡፡

❖ በጨረታ የእርዳታ እህልና ቁሳቁስ የሚያቀርቡ አቅራቢዎች ምርቱን ወደ ኮሚሽኑ ማዕከላዊ መጋዘኖች በራሳቸዉ ወጪ አጓጉዘዉ ገቢ የሚያደርጉ ሲሆን ከማዕከላዊ መጋዘኖች ወደ ክልል የማሰራጫ ጣቢያዎች ለማድረስና ለማጓጓዝ ደግሞ ግልጽ ጨረታ በማዉጣት የትራንስፖርት ድርጅቶች ተወዳድረዉ አሸናፊ የሆኑ የጭነት አገልግሎት በሚጠየቅበት ወቅት የሚያደርሱበት አሰራር ያለ መሆኑን ለዚህም ማሳያ ግልጽ ጨረታ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በማዉጣት እና በማወዳደር አሸናፊ የሆኑትን በመለየት በሚሰጣቸዉ የግዢ ትእዛዝና ውል መሰረት ለተረጂዎች እንዲላክ የሚደረግ መሆኑን

ገልፀዋል፡፡

90. የኮሚሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡-

❖ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ለአፋርና ሶማሌ ክልሎች የእርዳታ እህልና ቁሳቁስ ካጓጓዙ ትራንስፖርት አቅራቢዎች ጋር የተገባ የውል ስምምነት እና በውል ስምምነቱ መሰረት አገልግሎቶቱን ስለማቅረባቸው የሚያሳዩ ሰነዶች ያልቀረቡ በመሆኑ

❖ ለአፋርና ሶማሌ ክልሎች የሰብዓዊ እርዳታ እህልና ቁሳቁስ ያቀረቡ ትራንስፖርት አቅራቢ ድርጅቶች ዝርዝርና የውል ስምምነት ሰነድ ተጠይቆ ለተጠቀሱት ክልሎች የሰብዓዊ እርዳታ ለማድረስ ዕለት ደራሽ የዕርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት የሚባል ተቋም የሚጠቀሙ ስለመሆኑ መረጃ የቀረበ ቢሆንም ይህ ትራንስፖርት አቅራቢ ድርጅት ያለ ውድድር ከሌሎች ትራንስፖርት አቅራቢዎች የተመረጠና ኮሚሽኑም ከዚሁ ትራንስፖርት አቅራቢ ድርጅት አገልግሎት ሲፈልግ የውል ስምምነት የማይፈፅም በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

91. በመሆኑም የእርዳታ እህልና ቁሳቁስን ለማሰራጨት ከኮሚሽኑ መኪኖች በተጨማሪ ሌሎች ትራንስፖርት አቅራቢዎችን መጠቀም ሲያስፈልግ የሰብዓዊ እርዳታው በተፈለገው ጊዜና ሰዓት ለማሰራጨት ከትራንስፖርት አቅራቢዎቹ ጋር የውል ስምምነት የማይፈፀም ከሆነ የሰብዓዊ እርዳታው ሊስተጓጎልና በተረጂዎች ህይወት ላይ አደጋ ሊያደርስና ለብልሹ አሰራርም በር ሊከፍት ይችላል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

92. ከላይ በኦዲት ግኝቶች ላይ እንደተመለከተው በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት የሥራ አፈጻጸም የታሰበውን ዓላማ ማሳካት የተቻለ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት የአሠራር ግድፈቶች እና ክፍተቶች በመኖሩ የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡፡

- ኮሚሽኑ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ወገኖች የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት ተደራሽ መሆኑን የማረጋገጥባቸው አካባቢዎች መኖራቸው፣
- የተጨማሪ አልሚ ምግብ (በቆሎና አኩሪ አተር ቅይጥ CSB (corn, soya & bean) ከአምስት አመት በታች ላሉ ህፃናት፣ ለአጥቢና ነፍሰጡር እናቶች ብቻ መሰጠት የሚገባው ቢሆንም ለሁሉም ተረጂዎች ያለ ምንም ተጨማሪ መስፈርት እንዲሰጥና በአፋጣኝ እየተተካ አይደለም፣
- በናሙና ተመርጠው በታዩ መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚገኙ ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት፣ ነብሰጡር እና አጥቢ እናቶች የተጨማሪ አልሚ ምግብ (CSB) ካገኙ ወይም ከተቋረጠባቸው ከሁለት ዓመት በላይ የሆናቸው ተረጂዎች አሉ፡፡
- በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን በጎሮ ጉቱ እና ደደር በተባሉ መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ ተፈናቃዮች በአንድ መጋዘን ውስጥ ተጨናንቀው ተቀምጠዋል፣
- መብራት፣ ውሃ፣ ሽንት ቤት አገልግሎት የህክምና አገልግሎት የሌላቸው ወይም የማይሰሩ መጠለያ ጣቢያዎች መኖራቸው፣
- ለከፍተኛና ለዘርፈ-ብዙ አደጋዎች አስፈላጊ የሆኑ ሎጀስቲክስ/ ሄሊኮፕተር፣ ማሽነሪዎች፣ ጀልባዎች፣ ወዘተ የመሳሰሉ መሳሪያዎች አደጋ ሲከሰት በአፋጣኝ ለማቅረብና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል በኮሚሽኑ እንዲሁም በክልል አደጋ ስጋት አመራር ቢሮዎች ስትራቴጂ እና ሥርዓት አልተዘረጋም
- ከሶማሌ እና ኦሮሚያ ክልሎች በ2010 ዓ.ም በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ወገኖች ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጥር 2017 ዓ.ም ድረስ ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ ያልተደረገ በመሆኑ ለረጅም ጊዜ እርዳታ ጠባቂዎች እንዲሆኑ አድርጓል፡፡
- ኮሚሽኑ ለሰብዓዊ እርዳታ የሚውል በግዥም ሆነ በዕርዳታ ወደ መጋዘን የሚገቡ/በክምችት ያሉና የሚወጡ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በአያያዝ ጉድለት ለብልሽት የሚጋለጡበት እና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ለተረጂዎች የሚላክበትና የሚሰራጭበት ሁኔታ መኖሩ

- ኮሚሽኑ ለሰብዓዊ እርዳታ አገልግሎት የሚውል ዘላቂ ሀብት ለማሰባሰብ የሚያግዝ ፈንድ የሚቋቋምበት ጥናት ያላጠና እና የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ሃብት የማፈላለግ ስራ አላከናወነም፣
- ኮሚሽኑ በራሱ መጋዘኖችም ሆነ በሁሉም ክልሎች ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ አነስተኛ ክምችት መጠን (Minimum Stock Level) ተወስኖ የሚያዝበት ስርዓት አልዘረጋም፣
- በኮሚሽኑ የተለያዩ ማዕከላዊ መጋዘኖች የሚገኝ የእርዳታ እህል ለብልሽት በተጋለጠ መልኩ ያለ ፓሌት ፕላስቲክ ሸት ብቻ ተነጥፎበት መሬት ላይ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ የድሬደዋ ማዕከላዊ መጋዘን የጣሪያ ጥገና ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ ቢታቀድም ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ድረስ አለመከናወኑ፣
- የቅድመ ማስጠንቀቂያ የክስተት ሁኔታ መምሪያ ቴክኖሎጂዎችና የኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች ገና በዝግጅት ደረጃ የሚገኝ እና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ቴክኖሎጂዎችና ኮሚኒኬሽን መሣሪያዎች ያልተገጠመላቸው ክልሎች አሉ፣ በኮሚሽኑ የ10 ዓመት (2013-2022) መሪ ዕቅድ ወደ አመታዊ ዕቅድ ተመንዝሮ ስለመታቀዱ እንዲሁም በእቅድ ከተያዘ ደግሞ ስለመተግበሩ ማስረጃው ለኦዲት አልቀረበም፣
- በኮሚሽኑ እየተከናወኑ ያሉ የቀብሪዳሃር፣ የፍኖተሰላም እና የሆሳዕና የመጋዘን ግንባታዎች በተያዘላቸው ጊዜ እና በጀት እየተከናወኑ ባለመሆኑ መንግስትን ተጨማሪ 9,094,417,387.08 (ዘጠኝ ቢሊዮን ዘጠና አራት ሚሊዮን አራት መቶ አስራ ሰባት ሺ ሶስት መቶ ሰማንያ ሰባት) ብር ወጪ እንዲያወጣ አድርጓል፣ በተቋሙ የፕሮጀክት አፈፃፀም፣ የበጀት ግኝትንና አጠቃቀሙን ለመከታተል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት እንዲዘረጋ አልተደረገም፡፡
- ኮሚሽኑ ለክልሎች የሚላከው የእርዳታ እህልና ቁሳቁስ በተጠናው የሰብዓዊ እርዳታ ፈላጊ ቁጥርና በቀረበው ፍላጎት መሰረት የሰብዓዊ እርዳታ እህልና ቁሳቁስ መድረሱንና ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ በቂ የድጋፍና የቁጥጥር ስራ እያከናወነ አይደለም፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች የተላኩት ድጋፎች ለታለመላቸው ተረጂዎች ሳይደርሱ በገበያዎች፣ በሱቆች እና በወፍጮ ቤቶች ይታያሉ፣
- ኮሚሽኑ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ለማጓጓዝ ጨረታ ካሸነፉ ትራንስፖርት አቅራቢዎች ድርጅቶች ጋር እርዳታዎች በውሉ መሰረት እየተሠራጨ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- ኮሚሽኑ በዕቅዱ መሰረት ከተረጂዎች (ተፈናቃይ) ጋር ምክክርና ውይይት በዕቅዱ መሰረት አልተከናወነም፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

በመሆኑም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

93. የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት አፈጻጸም ሥርዓትን ውጤታማ ለማድረግ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ☞ ኮሚሽኑ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ወገኖች የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት ተደራሽ መሆኑን ለማረጋገጥ በየዓመቱ በዕቅዱ ውስጥ በማካተት ትኩረት ሰጥቶ የማረጋገጥ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ኮሚሽኑ ለክልሎች የሚላከው የእርዳታ እህልና ቁሳቁስ በተጠናው የሰብዓዊ እርዳታ ፈላጊ ቁጥርና በቀረበው ፍላጎት መሰረት የተሰራጨ መሆኑን እንዲሁም የሰብዓዊ እርዳታው ለተፈለገው አካባቢ መድረሱንና ለታለመለት ዓላማ መዋሉን የድጋፍና የቁጥጥር ስራ በመስራት ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ☞ ኮሚሽኑ የተጨማሪ አልሚ ምግብ (በቆሎና አኩሪ አተር ቅይጥ CSB (corn, soya & bean) ከአምስት አመት በታች ያሉ ህፃናትን፣ የአጥቢና የነፍሰጡር እናቶችን በበቂ ሁኔታ የሚያገኙበት እንዲሁም አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጥሮ ተጨማሪ መስፈርት ለሌሎች ተረጂዎች ከተከፋፈለ መልሶ የሚተካበት አሠራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግና ተግባራዊነቱን ኮሚሽኑ ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ የክትትልና የድጋፍ ስራውን በማጠናከር ወደ ክልሎች የሚላኩ እርዳታዎች ለሌላ ዓላማ እንዳይውሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ሊሰራና ሊከታተልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ☞ ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን በጎሮጉቱ እና ደደር ወረዳ መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ ተፈናቃዮች ለወረርሽኝ በሽታ ባልተጋለጠ ሁኔታ መጠለያ የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲፈጠር ሊያደርግ ይገባል፡፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በኦሮሚያ ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሮጉቱ እና ደደር ወረዳ የሚገኙ ባልታዩት እና ተመሳሳይ ችግር ያለባቸው የመጠለያ ጣቢያዎች ተፈናቃይ ወገኖች መብራት፣ ውሃ፣ ሽንት ቤት አገልግሎት እና መጠለያ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊሰራ ይገባል፡፡ የህክምና አገልግሎት የሌላቸው መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ ተፈናቃይ ወገኖች የህክምና አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አሰራር ሊዘረጋና መተግበሩን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ☞ ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ከሶማሌ እና ኦሮሚያ ክልሎች በ2010 ዓ.ም በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ እና በመጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ

ወገኖች ሆነ በሌሎች መጠለያ ጣቢያዎች ያሉ ተፈናቃዮች በቋሚነት ወደ መደበኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎቻቸው እንዲመለሱ የመልሶ ማቋቋም አገልግሎት የሚያገኙበት ስርዓት በመፍጠር ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ ሊያደርግ፣ የረጅም ጊዜ እርዳታ ጠባቂ እንዳይሆኑና በአምራችነት እንዲሳተፉ ስልት ነድፎ ሊተገብር ይገባል፡፡


- ለከፍተኛና ለዘርፈ-ብዙ አደጋዎች አስፈላጊ የሆኑ ሎጀስቲክስ/ ሄሊኮፕተር፣ ማሽነሪዎች፣ ጀልባዎች፣ ወዘተ የመሳሰሉ መሳሪያዎች ሲከሰቱ በአፋጣኝ ለማቅረብና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ፣ በኮሚሽኑ እንዲሁም በክልል አደጋ ስጋት አመራር ቢሮዎች ደረጃ እንዲሟሉ ወይም ለአገልግሎት ሲያስፈልጉ ከሌሎች አካላት በውሰትም ሆነ በኪራይ የሚገኙበት ስትራቴጂ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ እንደ አገር በራስ አቅም ችግሮችን ለመቋቋም የሚረዳ ሀብት ለማሰባሰብ በጥናት ላይ የተመሰረተ ለድንገተኛ አደጋ መከላከያ ሥራ የሚውል ፈንድ ለማቋቋም የመነሻ ሃሳብ ሊያዘጋጅና ለሚመለከተው አካል በማጸደቅ ሊያቋቁም ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ሃብት የማሰባሰብ ሥራ በማከናወን ከውጭ ለጋሽ አካላት ከሚገኘው ድጋፍ በተጨማሪ በአገር ውስጥ ሀብት በቋሚነት የሚሰበሰብበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግና ኮሚሽኑ በ10 ዓመቱ (2013-2022) መሪ ዕቅድ መሰረት ሀብት ማሰባሰብ ይጠበቅበታል፡፡
- ኮሚሽኑ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ አነስተኛ ክምችት የሚያዝበት ስርዓት ዘርግቶ በራሱም ሆነ በክልል አደጋ ስጋት መጋዘኖች ተግባራዊ እንዲደረግ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ ለሰብዓዊ እርዳታ የሚውል ዕርዳታ ወደ መጋዘን ሲገባም ሆነ ለተረጂዎች ወጪ ሲደረግ አስፈላጊው ምርመራ ወይም ፍተሻ መደረጉን ሊያረጋግጥ፣ የድሬደዋ ማዕከላዊ መጋዘን የጣሪያ ጥገና ተከናውኖ በዘላቂነት ችግሩ ሊፈታ፣ እንዲሁም በኮሚሽኑ የተለያዩ ማዕከላዊ መጋዘኖች የሚገኝ የእርዳታ እህል ለብልሽት እንዳይጋለጥ ደረጃውን
- የጠበቀ ከመሬት ከፍ ባለ ነገር ወይም በፓሌት እንዲቀመጥ ሊያደርግ፣ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የቅድመ ማስጠንቀቂያ የክስተት ሁኔታ መምሪያ ቴክኖሎጂዎችና የኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች ገና በዝግጅት ደረጃ የሚገኙ የቅድመ ማስጠንቀቂያ የክስተት ሁኔታ መምሪያ ቴክኖሎጂዎችና የኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች፣ የSituation room ግንባታ ወደ ሙሉ ትግበራ እንዲገቡ ሊደረግ የሚገባና እና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ቴክኖሎጂዎችና ኮሚኒኬሽን መሣሪያዎች ያልተገጠመላቸው ክልሎች ዕቅድ

ተይዞላቸው ሊሟላላቸው የሚገባና በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች የቅድመ ማስጠንቀቂያ ትግበራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተደግፎ ሊከናወን ይገባል፡፡

- ☛ ኮሚሽኑ የቀብሪዳሃር፣ የፍኖተሰላም እና የሆሳዕና የመጋዘን ግንባታዎች በተያዘላቸው ጊዜ እና በጀት እንዲጠናቀቁና ከተቋራጮችና ከአማካሪ ድርጅቶች ጋር ያጋጠሙ ችግሮች ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር እንዲፈቱ በማድርግ እና በተገባው ውል መሰረት ስራው እየተሰራ ስለመሆኑ ተገቢውን የድጋፍና የክትትል ስራ ሊሰራ እና ለታለመላቸው ዓላማ  አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ☛ ኮሚሽኑ በ10 ዓመቱ (2013-2022) መሪ ዕቅድ መሰረት በየአመቱ የሃብት ማሰባሰቢያ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ሃብት የማሰባሰብ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ☛ ኮሚሽኑ በሁሉም የሃገሪቱ አካባቢዎች ባሉ መጠለያ ጣቢያዎች በአካል በመገኘት ከተረጂዎች (ተፈናቃይ) ወገኖች ጋር ምክክርና ውይይት በማካሄድ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ☛ ኮሚሽኑ የእርዳታ እህልና ቁሳቁስ ለማጓጓዝ በጨረታ ከለያቸው ትራንስፖርት አቅራቢ ድርጅቶች ጋር የውል ስምምነት እንዲፈረምና በውሉ መሠረት ተግባራዊ መደረጉና ሊከታተል ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የበላይ ሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም መረጃ የሰበሰብንባቸው የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1: ተቋማዊ መዋቅር



# አባሪ ሁለት፡ የመመዘኛ መስፈርቶች

**የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት፡- የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን**

**የኦዲቱ አካባቢ፡ የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት አፈፃፀም ውጤታማነትን መገምገም፤**

| የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| 1. ኮሚሽኑ ሰብዓዊ ዕርዳታ ለማቅረብ የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም | 1. ኮሚሽኑ ከአደጋ ስጋትና ክስተት እንቅስቃሴዎች ጋር በተያያዘ የሚሰበሰቡ መረጃዎች በጾታ፣ በእድሜ በስም እና ሌሎች የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የአደጋ ተጋላጭነት አመልካቾች ተለይተው ሊሰበሰቡና ሊተነተኑ ይገባል፡፡ |
| | 2. ኮሚሽኑ የቅድሚያ ቅድሚያ ትኩረት ምላሽ የሚገባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ለመለየት የሚያስችል መስፈርት ከባለድርሻ አካላት ጋር በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 3. ኮሚሽኑ ምግብ ነክ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን ወደ ቅርንጫፍ (ማዕከላዊ) መጋዘኖች ለማጓጓዝ ለትራንስፖርት አቅራቢዎች ጨረታ በማውጣት ከአሸናፊዎቹ ትራንስፖርት አቅራቢ ድርጅቶች ጋር በመፈራረም በገቡት ውል መሰረት አገልግሎቱን ማቅረባቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 4. ኮሚሽኑ ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር የተያዙ የተለያዩ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ክምችቶች በመጠቀሚያ ጊዜያቸው ለይቶ ሊመዘግብና ለስርጭት ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ |
| | 5. ኮሚሽኑ ለሰብዓዊ እርዳታ የሚውል በግዥም ሆነ በዕርዳታ ወደ መጋዘን የሚገቡ/በክምችት ያሉና የሚወጡ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች የጥራት እስፔሲፊኬሽን በማዘጋጀት ጥራታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 6. ኮሚሽኑ ለሰብዓዊ እርዳታ ስራ የሚውል ለአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ፈንድ በቋሚነት የሚሰባሰብበት ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 7. ኮሚሽኑ ለዕለት ድጋፍ የሚውል አስፈላጊ የሆነ የተሟላ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ አነስተኛ ክምችት የሚያዝበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 8. ኮሚሽኑ በተለያዩ መጋዘኖች የሚገኝ ክምችትን ከብልሽት የሚከላከልበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 9. ኮሚሽኑ ለምግብ ጥራት መመርመሪያ አገልግሎት ስራ ላይ የሚዉሉ የተለያዩ መሳሪያዎች በየጊዜው ካሊብሬት ሊደረጉና በትክክል መስራታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 10. ኮሚሽኑ የተፈጥሮ አደጋዎች የትኛውን የህብረተሰብ ክፍል፣ መቼ እንደሚያጠቁ የድግግሞሽ መጠንና በምን ሁኔታ እንደሚከሰቱ፣ የጥቃቱን መጠን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በዝርዝር በማጥናት የቅድመ ጥንቃቄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| | 11. ኮሚሽኑ ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር የሚያገለግሉ የአደጋ ጊዜና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ዘመናዊ የመገናኛ መሳሪያዎች እና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት በመዘርጋት አፋጣኝ ውሳኔ |

| | |
|---|---|
| | ለመስጠት የሚያስችል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 12. ኮሚሽኑ የአደጋ ጊዜ መረጃ ልውውጥና የመረጃ ቅብብሎሽ (Disaster Information) ወጥ በሆነ መንገድ ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት የሚረዳ መመሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 13. ኮሚሽኑ ለከፍተኛና ለዘርፈ-ብዙ አደጋዎች አስፈላጊ የሆኑ ሎጅስቲክስ/ በአፋጣኝ ለዕርዳታ ፈላጊዎች የሚደርስበት የትራንስፖርት አቅርቦት ስርዓት በመዘርጋት የአደጋ ስጋት አመራርን ሊተገብር ይገባል፡፡ |
| | 14. ኮሚሽኑ ለአደጋ ስጋት አመራር በጎ ፈቃደኞችን ለማሰልጠን የሚረዳ የማሰልጠኛ ማንዋል ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 15. ኮሚሽኑ የሰብዓዊ ድጋፍ አቅርቦቱ በበጎ ፈቃደኞች የሚታገዝበትን የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 16. ኮሚሽኑ ለክልሎች የሚላከው የእርዳታ እህልና ቁሳቁስ በተጠናው የሰብዓዊ እርዳታ ፈላጊ ቁጥርና በቀረበው ፍላጎት መሰረት የሰብዓዊ እርዳታ እህልና ቁሳቁስ መድረሱንና ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ክትትል በማድረግ የድጋፍና የቁጥጥር ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| 2. ሚሽኑ በሌሎች አጋር አካላት የሚከናወኑ የሰብዓዊ ዕርዳታ ተግባራትን ለማስተባበር፣ ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም | 17. ኮሚሽኑ ከቀረጥ ነፃ ድጋፍ የሚገቡ እና መንግስታዊ ባልሆኑ የእርዳታ ድርጅቶች የሚሰራጩ ምግብ ነክ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ እርዳታዎች በድርጅቶቹ አማካኝነት ሲሰራጩ ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 18. ኮሚሽኑ የዕቅድ አፈፃፀሙን ለመለካትና ሊደረስበት የታሰበውን ግብ መከናወኑን ለመገምገም የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 19. ኮሚሽኑ የአገልግሎት አሰጣጡን በታቀደው መሰረት መከናወኑን በየጊዜው ሊገመግምና ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 20. ኮሚሽኑ የሰብዓዊ ዕርዳታ ሲያሰራጭ የአጥቢ፣ ነብሰ ጡር እናቶችና ህፃናት ፍላጎቶችን ያገናዘበ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 21. ኮሚሽኑ አጥቢ፣ ነብሰ ጡር እናቶችና ህፃናት በተዘረጋው ስርዓት የተመጣጠነ ምግብ ስለ ማግኘታቸውና ስለመጠቀማቸው ዝርዝር መረጃ ሊያደራጅና ለሚመለከተው ሊያሳውቅ ይገባል፡፡ |
| | 22. ኮሚሽኑ የእርዳታ እህልና ቁሳቁስን ያለ አግባብ ላልተገባ ዓላማ እንዳይውል ለመከታተል የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 23. ኮሚሽኑ መሪ ሴክተር ተቋማት በአጭር፣ በመካከለኛና ረዥም ጊዜ ዕቅዳቸው ውስጥ የአደጋ ስጋት ስራ አመራርን ማካተታቸውን እና ይህንንም መከታተል የሚቻልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| 3. ሚሽኑ የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦትና ስርጭት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበትንና መረጃ የሚለዋወጥበትን የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም | 24. ኮሚሽኑ የየአመት ዕቅድ አፈፃፀሙን ከባለድርሻ አካላት፤ ከአጋር አካላት እና ከክልሎች ጋር በጋራ ሊገመግም ይገባል፡፡ |
| | 25. .ኮሚሽኑ፣ የተገልጋዮች እርካታን ለመለየት በየስድስት ወራቱ የዳሰሳ ጥናት ሊያካሂድ ይገባል፡፡ |
| | 26. ኮሚሽኑ በአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር ዙሪያ ለክልሎችና ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 27. ኮሚሽኑ ከትራንስፖርት አቅራቢ ድርጅቶች፣ ከተረጂዎች (ተፈናቃይ ወገኖች) እና ከክልሎች ጋር ምክክርና ውይይት በማድረግ በዕርዳታ አቅርቦቱ እና ስርጭቱ ላይ ችግር እንዳይፈጠር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |

## አባሪ 3፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የመስክ ጉብኝት የተደረገባቸው እና በኢሜል መጠይቅ የቀረበላቸው

1. **የመስክ ምልከታ የተደረገባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች (ማዕከላዊ መጋዘን)**
   - ✓ አዳማ ቅ/ጽ/ቤት (ማዕከላዊ መጋዘን)
   - ✓ ድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤት (ማዕከላዊ መጋዘን)
   - ✓ ሽንሌ ቅ/ጽ/ቤት (ማዕከላዊ መጋዘን)
2. **የመስክ ምልከታ የተደረገባቸው የክልል አደጋ ስጋት አመራር ቢሮዎች**
   - ✓ ቡሳ ጎኖፋ (የኦሮሚያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን)
   - ✓ በሶማሌ ብ/ክ/መ/ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን
   - ✓ በሐረሪ ብ/ክ/መ/ የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ የምግብ ዋስትና አደጋ መከላከል ጽ/ቤት
   - ✓ በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን
3. **የመስክ ምልከታ የተደረገባቸው መጠለያ ጣቢያዎች**
   - ✓ ቆሎጂ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ (ሶማሌ ክልል)
   - ✓ ሐማሬሳ መጠለያ ጣቢያ (ሐረሪ ክልል)
   - ✓ በኦሮሚያ ምስራቅ ሐረርጌ ዞን በካራሚሌ ከተማ የሚገኘው ኒጊዴ ተፈናቃዮች መጠለያ ካምፕ
   - ✓ በኦሮሚያ ምስራቅ ሐረርጌ ዞን በደደር ወረዳ ከሚገኙት ስድስት መጠለያ ጣቢያዎች መካከል ሶስቱ (ኒው ጎልማሳ ፣አልድ ጎልማሳ እና ኢ.ዲ.ዲ.ሲ የተሰኙ) መጠለያ ጣቢያዎች
4. **በኢሜል መጠይቅ የተላከላቸው የክልል አደጋ ስጋት አመራር ቢሮዎች**
   - ✓ በትግራይ ብ/ክ/መ/ለአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
   - ✓ በአፋር ብ/ክ/መ/ለአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
   - ✓ በአማራ ብ/ክ/መ/ለአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ኮሚሽን
   - ✓ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን
   - ✓ በጋምቤላ ህ/ብ/ክ/መ/ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን
   - ✓ በደቡብ ኢትዮጵያ ህ/ክ/መ/ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን
   - ✓ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ህ/ብ/ክ/መ/ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን
   - ✓ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህ/ክ/ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን
   - ✓ በሲዳማ ብ/ክ/መ/ ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን

# አባሪ 4 -የተከለሱ ሰነዶች

## በኦዲት ወቅት የተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች ዝርዝር

1. የብሔራዊ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 363/2008 ፣
2. የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የአስር ዓመት ዕቅድ (ከ2013-2022 ዓ.ም)፣
3. ብሔራዊ የአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ (2005ዓ.ም)፣
4. የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲ (2016 ዓ.ም)፣
5. ረቂቅ የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር አዋጅ፣
6. በፌደራልና ክልል መንግስታት በጋራ የተዘጋጀው የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ እርዳታ ቁሳቁሶች አስተዳደር ማንዋል (የሰብዓዊ የዕለት ዕርዳታ እና የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም)
7. የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 284/2005 ዓ.ም፣
8. የተበላሸ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ከክምችት የሚወገዱበት የውስጥ አሰራር መመሪያ ቁጥር 3/2013 ዓ.ም፣
9. የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች የክምችና ስርጭት አስተዳደር፣
10. የተባይ ክትትልና ቁጥጥር የውስጥ አሰራር መመሪያ ቁጥር 1/2013ዓ.ም፣
11. ከ2013-2016 በጀት ዓመት የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ዕቅድ፣
12. ከ2013-2016 ዓ.ም የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች
13. የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ (2013-2022)

## አባሪ 5፡ የመጠለያ ጣቢያዎችና የተረጂ ወገኖች ብዛት በክልል

| ተ.ቁ | ክልል | የጣቢያዎች ብዛት | የተረጂ ወገኖች ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ሶማሌ | 560 | 1,100,636 |
| 2 | ኦሮሚያ | 778 | 881,984 |
| 3 | ትግራይ | 676 | 878,325 |
| 4 | አማራ | 259 | 174,608 |
| 5 | አፋር | 90 | 81,791 |
| 6 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 82 | 74,697 |
| 7 | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 180 | 49,262 |
| 8 | ሲዳማ | 58 | 36,447 |
| 9 | ጋምቤላ | 23 | 26,723 |
| 10 | ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | 23 | 6,891 |
| 11 | ሐረሪ | 9 | 2,220 |
| | ድምር | 2738 | 3,313,584 |

## አባሪ 6፡ የመጠለያ ጣቢያዎችና የተረጂ ወገኖች ብዛት በዕድሜ

| ዕድሜ | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| ከ 0-4 | 245,588 | 243,702 | 489,290 |
| ከ 5-14 | 528,695 | 586,682 | 1,115,377 |
| ከ 15-17 | 80,613 | 89,892 | 170,505 |
| ከ 18-59 | 671,915 | 764,807 | 1,436,722 |
| ከ 60 በላይ | 54,875 | 39,929 | 94,804 |
| | 1,581,686 | 1,725,012 | 3,306,698 |

## አባሪ 7. ዕድሜያቸው ከ0-4 የሆኑ ተፈናቃይ ህጻናት ብዛት በክልል

| ክልል | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| አፋር | 6,415 | 6,636 | 13,051 |
| አማራ | 8,951 | 8,521 | 17,472 |
| ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 4,779 | 5,303 | 10,082 |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 2,261 | 2,319 | 4,580 |
| ጋምቤላ | 3,054 | 3,223 | 6,277 |
| ሐረሪ | 121 | 90 | 211 |
| ኦሮሚያ | 65,917 | 75,221 | 141,138 |
| ሲዳማ | 2,850 | 2,862 | 5,712 |
| ሶማሌ | 110,039 | 97,775 | 207,814 |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | 460 | 495 | 955 |
| ትግራይ | 40,741 | 41,257 | 81,998 |
| ድምር | 245,588 | 243,702 | 489,290 |

# አባሪ 8፡ ለመጋዘን ግንባታ የተመደበ የካፒታል በጀት

| የፕሮጀክቱ ርዕስ | 2010 በጀት አመት | 2011 በጀት አመት | 2012 በጀት አመት | 2013 በጀት አመት | 2014 በጀት አመት | 2015 በጀት አመት | 2015 በጀት አመት | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የመጋዘን ዲዛይንና የአፈር ምርመራ ፕሮጀክ | 7,000,000 | 7,300,000 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 14,300,000 |
| የፍኖተ ሰላም የመጋዘን ግንባታ | 223,914,000 | 244,584,400 | 205,849,000 | 232,849,000 | 284,266,500 | 179,500,000 | 100,000,000 | 1,470,962,900 |
| የሆሳዕና የመጋዘን ግንባታ | 208,854,000 | 241,605,170 | 205,000,000 | 205,000,000 | 284,266,500 | 203,500,000 | 100,000,000 | 1,448,225,670 |
| የቀብሪደሐር የመጋዘን ግንባታ | 80,464,000 | 55,959,540 | 104,000,000 | 104,000,000 | 131,466,800 | 280,000,000 | 120,000,000 | 875,890,340 |
| ጠቅላላ ድምር | 520,232,000 | 549,149,110 | 514,849,000 | 541,849,000 | 699,999,800 | 840,000,000 | 320,000,000 | 3,809,378,910 |

# አባሪ 9፡የካፒታል በጀት አፈፃፀም

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ስም | ውል የተገባበት የገንዘብ መጠን (በብር) | የተጀመረበት ቀንና ዓ.ም | የሚጠናቀቅበት ቀንና ዓ.ም | ግንባታውን የሚያከናውነው ስራ ተቋራጭ | የተከፈለ ቅድመ ክፍያ (በብር) | ፊዚካል አፈፃፀም እስከ ህዳር 30/2017 ዓ.ም (በመቶኛ) | ፋይናንሻል አፈፃፀም እስከ ህዳር 30/2017 ዓ.ም (በመቶኛ) | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ፍኖተሰላም የእህል መጋዘን ምድረ ግቢና ሌሎች ተዛማች ህንፃዎች ግንባታ | 6,555,000,000.00 | Apr 28,2023 | 2 ዓመት | ኦቪድ ኮንስትራክሽን ኋላ.የተ.የግ.ማህበር | 655,500,000.00 | 49.24 | ----- | የመጀመሪያው ውል ካበቃ ከ2 ዓመት በኃላ የተገባ ውል |
| 2 | ቀብሪድሃር የእህል መጋዘን ምድረ ግቢና ሌሎች ተዛማች ህንፃዎች ግንባታ | 626,718,375.66 | May 31,2024 | 1 ዓመት | ስሪኤም ኢንጂነሪንግና ኮንስትራክሽን ኋላ.የተ.የግ.ማህበር | 50,000,000.00 | 71.5 | 46.92 | የመጀመሪያው ውል ካበቃ ከ3 ዓመት በኃላ የተገባ ውል |
| 3 | ሆሳዕና የእህል መጋዘን ምድረ ግቢና ሌሎች ተዛማች ህንፃዎች ግንባታ | 4,305,357,765.23 | June 5,2024 | 2 ዓመት | ጂንግዚ የውሃና ሃይድሮፓወር ኮንስትራክሽን ኮ.ሊሚትድ ጥምረት ከኦቪድ ኮንስትራክሽን ኋላ.የተ.የግ.ማህበር | 598,317,332.02 | 34.47 | 13.89 | የመጀመሪያው ውል ካበቃ ከ1 ዓመት በኃላ የተገባ ውል |